# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 118 ታኅሣሥ 28 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትሪያርክ


ብፁእ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ


ፓስተር ጻድቁ አብዶ


ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ

# ምዕመናን በዓሉን የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ እንዲያከብሩ የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ

ሄለን ወንድምነው እና ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ሲያከብር በተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች በመደገፍ ሊሆን እንደሚገባ የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ።

አባቶቹ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ያሉት ግጭቶችና አለመግባባቶች ተወግደው ሰላም እንዲሰፍንና ሀገራዊ አንድነት እንዲረጋገጥ ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ

ምዕመናን በዓሉን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የክርስቶስን ልደት ስናከብር በልደቱ ካገኘነው በረከትና መዳን ቀጥለን ዓለም የተቀየረበትን መንገድ ማጤን አለብን”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የክርስቶስን ልደት ስናከብር በልደቱ ካገኘነው በረከትና መዳን ቀጥለን ዓለም የተቀየረበትን መንገድ ማጤንና እኛም የምንሄድበትን መንገድ መገምገም አለብን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዛሬ የሚከበረውን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ትናንት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት አስተላልፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የክርስቶስ የልደት በዓል ሁለት አስደናቂ ነገሮች የተፈጸሙበት ነው ። የተጠበቀው ባልተጠበቀው መንገድ የመጣበት እና ያልተጠበቁት ባልተጠበቀ ቦታ የተገኙበት ነው። የዓለምንና የሀገርን ታሪክ የሚቀይሩ ነገሮች በተለመዱና በሚጠበቁ መንገዶች ላይመጡ ይችላሉ። የክርስቶስን ልደት ስናከብር በልደቱ ካገኘነው በረከትና መዳን ቀጥለን ዓለም የተቀየረበትን መንገድ ማጤንና እኛም የምንሄድበትን መንገድ መገምገም አለብን።

“የክርስቶስን ልደት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ስምምነቱን የማይደግፉት ኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ በድህነት እንዲኖሩ የሚፈልጉ አካላት ብቻ ናቸው

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና የሶማሊ ላንድን የባሕር በር ስምምነት የማይደግፉት በድህነት እንድንኖር የሚፈልጉ አካላት ብቻ ናቸው ሲሉ በኢትዮጵያ የሶማሊ ላንድ ኤምባሲ ምክትል የሚሲዮን መሪ በርከድ መሀሙድ (ዶ/ር) ገለጹ።

በርከድ መሀሙድ (ዶ/ር) ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያና የሶማሊ ላንድ የተፈራረሙት የባህር በር ስምምነትን አለመደገፍ በእራሱ በቀሪው ጊዜያችሁ በድህነት ውስጥ ቆዩ የሚል መልዕክት ያለው ነው።

የኢትዮጵያና የሶማሊ ላንድ ስምምነት ከ130 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎችን ሕይወት ለማሻሻልና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ነው ያሉት ዶክተር በርከድ፤ ስምምነቱን እንዳይተገበር ፍላጎት ያላቸው አካላት ሁሉ በእነዚህ ዜጎች ቀጣይ እጣ ፋንታ ላይ መጥፎ ጥላ እንዲያጠላ ምኞትና ፍላጎት ያላቸው ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ቀጣናው በኢኮኖሚ እንዲያድግም ሆነ የማሪታይም ጸጥታው ዘርፍ እንዲጠናከር የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ ወገኖችም ሆኑ የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ሀገራት ስምምነቱን

ስምምነቱን የማይደግፉት.... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ሀዲስ አብርሃ


በርከድ መሀሙድ (ዶ/ር)

## በመቅደላ ጦርነት ወቅት የተዘረፉ ከ10 በላይ ጽላቶችን ለማስመለስ ጥረት እየተደረገ ነው

ገጽ 4


eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

Medhin Decor

የተንጣለለ ድንቅ የሰርግ አዳራሽ ከነ ሙሉ የውበት ስራ
የተሟላ የምግብ ዝግጅት ከሙሉ መስተንግዶ ጋር
Medhin Decor
ለሠርግ ለልደት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች
አድራሻ 1ኛ በሌ ጌቱ ኮሜርሻል ጀርባ
2ኛ ከቃሊቲ ማሰልጠኛ አለፍ
ብሎ ቆርኪና ጣሳ ፋብሪካ ገባ ብሎ
Contact Us 0911222993/ 0911208918

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

ቴክኖ ፋይበር
Technofiber
Techno Fiber


የምንሰጣቸው አገልግሎት
• ማንኛውንም በፋይበር ግላስ የሚሰሩ ነገሮችን በደንበኞች ትእዛዝ እናመርታለን
• የፋይበር ግላስ ጥሬ እቃዎችን አስመጥተን በጅምላም ሆነ በችርቻሮ እናከፋፍላለን
• ለፋይበር ሥራ የሚሆኑ የተለያዩ ፍሬም ፣ የታንከር እንዲሁም የተለያዩ ምልዶችን እንሽጣለን
• በተጨማሪም በዚህ ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ውስን ወጣቶች የነፃ ሥልጠና እንሰጣለን
+251 940526393/+251948969696

AfriSky PLC
ETHIOPIA


0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory


ዜና

# ‹‹ከተባበርንና አብረን ከቆምን የሕዝባችንን የኑሮ ጫና ማቃለል እንችላለን ››

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ታደሠ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- ሀብታችንና ሃሳባችንን አንድ አድርገን ከተባበርና አብረን ከቆምን የሕዝባችን የኑሮ ጫና ማቃለል እንችላለን ሲሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከተማ አስተዳደሩ የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ ለሶስት ሺህ ዝቅተኛ የገቢ ላላቸው የመንግሥት ሠራተኞችና ነዋሪዎች በትናትናው ዕለት ማዕድ አጋርቷል።

የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ የተደረገውን ማዕድ ማጋራት መርሀ ግብር አስመልክተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ ሀብታችንና ሃሳባችንን አንድ አድርገን ከተባበርና አብረን ከቆምን የሕዝባችን የኑሮ ጫና ማቃለል ብቻ ሳይሆን በርካታ ቁም ነገር መሥራት እንችላለን። በዚህ መነሻ መሠረትም በተባበረ ክንድ የነዋሪዎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል በቅንጅት እየሠራን ነው ።

በዓል በመጣ ቁጥር የምናደርገው ማዕድ የማጋራት ተግባር የበርካቶችን ጎጆ ገመናን የምንመለከትበትና ያለውን የኑሮን ጫና ለማቃለል በይበልጥ ለመሥራት የምንነሳሳበት አጋጣሚ ነው ብለዋል።

መርሀ ግብሩ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ ምንም ገቢ የሌላቸውና በተለያየ መንገድ ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችንን ከጎናቸው እንደሆንን የሚያሳይ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ማዕድ ብቻ አይደለም የምናጋራችሁ በማዕዱ ውስጥ ፍቅራችንን፣ አክብሮነታችንን፣ ለወገኖቻችን ያለንን ርህራሄና ሠርቶ ለመለወጥ ያለንን ትጋት የምናሳይበትም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ ከ263 ሺህ በላይ የሚሆኑ የመዲናዋ ነዋሪዎች ማዕድ ተጋርተዋል፤ ማዕድንም ለማጋራት 750 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል ያሉት ከንቲባዋ፤ ከከተማ አስተዳደሩ በጀት አንድም የወጣ ሳንቲም የለም፤ ሀብቱ የተሰበሰበው ከባለሀብቶች ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረተሰብ ተሳትፎና የበጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብረሃም ታደሰ በበኩላቸው፤ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በክፍለ ከተሞች፣ በወረዳዎችና በማዕከላት ደረጃ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች፣ የሀገር ባለውለታዎችና የአረጋውያን ማዕድ ተጋርተዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ማዕድ የማጋራት በጎ ተግባር ፍቅርን፤ አብሮነትን፣ መተባበርንና መተጋገዝን የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመው፤ ስንደጋገፍ ችግራችንን መፍታት እንችላለን ብለዋል ።

የማህበረሰቡ ደስታ ደስታችን ነው፤ አብሮነቱና ደስታው ይበልጥ እንዲያድግ እንሠራለን ሲሉ አመልክተዋል።

በከተማ አስተዳደሩ የገና በዓል ማዕድ ተጋሪ የሆኑት ወይዘሮ ቅድስት ክንዱ፤ በተደረገላቸው ድጋፍ እንደተደሰቱና ድጋፉም የኑሮ ጫናቸውን እንዳቀለለላቸው ተናግረዋል።

‹‹በዓሉን ለማክበር የሚያስችል የገቢ አልነበረኝም ፤ አሁን በተደረገልኝ ድጋፍ በዓሉን በደስታ አከብሬው እውላለሁ ›› ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹የተደረገልን ድጋፍ በዓል ካለማክበር ወደ ማክበር አሸጋግሮናል ›› ሲሉ ሌላኛዋ የማዕዱ ተጋሪ ወይዘሮ ትግስት ተሾመ ተናግረዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ያለብንን ችግር ታች ድረስ ወርዶ፣ ተረድቶ ባደረገልን ድጋፍ ተደስቻለሁ፤ ተጠናክሮም ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

# የ “ስማርት ኮርት” አገልግሎት ህብረተሰቡ ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኝ ያስችላል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በቴክኖሎጂ የታገዘ ዳኝነት (“ስማርት ኮርት”) አገልግሎት የሚስተዋሉ የህብረተሰብ ችግሮችን ከመሠረቱ በመፍታት ተገቢውን የፍትህ አገልግሎት እንዲያገኝ እንደሚያደርግ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ አስታወቁ።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የ“ስማርት ኮርት” ማብሰሪያ ፕሮግራም አካሂዷል።

ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ እንደገለጹት፤ በ“ስማትር ኮርት” የተደገፈ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት መጀመሩ እንደ ሀገር ተስፋ ሰጪ ምእራፍ ላይ መሆናችንን ያመለክታል። በተለይ ሀገራዊ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂክ እቅድ ሙሉ በሙሉ ስኬታማ እንደሚሆን እርግጠኛ የሚያደርግ ነው።

እንደ አፈ ጉባዔው ገለጻ፤ በተለያዩ ጊዜያት የሀገራችንን የዳኝነት ሥርዓት ለማሻሻል በርካታ የለውጥ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ቢሆንም ዘርፉ ያለበትን የቅልጥፍና፣ የተደራሽነት፣ የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና የተዓማኒነት ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ መፍታት አለመቻሉን ገልጸዋል።

ለዚህም ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ሙሉ ለሙሉ በሰዎች ንክኪ የተመሠረተ መሆኑን ጠቁመው፤ የሰው ሰራሽ አስተውሎትን ጨምሮ “ስማርት ኮርት” አገልግሎት በዳኝነት አሠጣጥ የሚስተዋሉ የህብረተሰብ ችግሮችን ከመሠረቱ በመፍታት ተገቢውን የፍትህ አገልግሎት ለመስጠት ትልቅ አቅም እንደሚሆን አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ታገሰ ጫፎ ገለጻ፤ በዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጅክ እቅድ ውስጥ ለማሳካት ከታለሙት ዋና



አቶ ታገሰ ጫፎ

ዋና ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ለዜጎች የሚሰጡ የመንግሥት አገልግሎቶችን የዘመኑ፣ ከአካላዊ ንክኪ የጸዱና ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ይህን ለማድረግም መንግሥትም ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ ርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። የዳኝነት አገልግሎት በአንድ ሀገር ውስጥ የሕግ በላይነት እንዲከበር፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን፣ የሠብዓዊ መብቶች ጥበቃ እንዲረጋገጥ፣ የሀገር ልማት እንዲሳካ ወሳኝ በመሆኑ በቴክኖሎጂ መደገፍ እንዳለበት ገልጸዋል።

የዳኝነት አገልግሎትን ለማሳለጥ የበለጸገው “ስማርት ኮርት” በራስ በጀትና የባለሙያዎች አቅም የለማ መሆኑ ሀገራችን እምቅ አቅም እንዳላት ያሳያል። በመንግሥት የተያዘው ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማ እየሆነ መሆኑን ያረጋግጣል። በፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎቶች የዜጎች ዋስትና በመሆናቸው ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ይህ በተግባር ውጤታማ የሚሆነው የዳኞች አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ጥራትና ተዓማኒነት ያለው ሲሆን ብቻ መሆኑን ገልጸዋል።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት በበኩላቸው፤ የፍትህ መጓደል ያልተረጋጋ ማህበረሰብ እንዲፈጠርና የሕግ የበላይነት እንዲሸረሸር አስተዋፅኦ ያደርጋል። ይህን የሀገርን ሰላም እንዳይሸረሸር ፍርድ ቤቶች የዜጎችን ፍትህ ማርካት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

የፍትህ መጓደል የሕዝብ የረጅም ጊዜ ጥያቄዎች ሆነው ዘልቀዋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዓለም በደረሰበት የዕድገት ደረጃ የዳኝነት አገልግሎት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ መስጠት መደበኛ አሠራር ሆኗል። በዚህ ረገድ በሀገራችን የተደረገው መጠነኛ ጥረት አገልግሎቱን ለማሻሻል በተወሰነ ደረጃ ከመደገፍ ባለፈ ቴክኖሎጂ የሚያስገኘውን ትሩፋት በሙሉ ለመጠቀም አልተቻለም ነው ያሉት።

የፍትህ አሠራሩን ለማሻሻል መጠነ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የተመረቀው ስማርት ኮርት የመጀመሪያው በረከት ነው። ቀሪ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የዳኝነት አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ተደራሽ እንዲሆን እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

የተመረቁት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ንግግርን ወደ ጹሑፍ የሚቀይር ሥርዓት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ችሎት፣ የውይይት መለዋወጫ ሮቦትና መረጃ መስጫን ያካተተ ነው። ወደ ሥራ ሲገቡ በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው ፍትህ ከመስጠት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችን እንደሚቀንስ ይታመናል ብለዋል።

# ከኃይማኖት ተቋማት የሚለቀቁ ከደረጃ በላይ የሆኑ ድምጾችን በጋራ መከላከል ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ከኃይማኖት ተቋማትና በኃይማኖት ተቋማት ስም የጎዳና ላይ ስብከትና ልመና የሚውል ከደረጃ በላይ የሆኑ የድምጾችን ከኃይማኖት ተቋማት ጋር በጋራ መከላከል እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ከአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ጋር በመተባበር ከደረጃ በላይ የሆኑ የድምፅ ብክለት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ሰሞኑን ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ በከተማው ከእምነት ተቋማት ውስጥ የሚወጡ ድምጾች ከደረጃ በላይ ናቸው። እነዚህን ድምጾች ጉዳት እንደሚያደርሱ በመረዳት ለመፍትሄው ከኃይማኖት ተቋማት ጋር በጋራ መሥራት አስፈላጊ ሆኗል።

የድምጽ ብክለት ምንጮች በዋነኝነት የትራንስፖርት፣ ግንባታና ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ ከንግድ እና ከመኖሪያ ቤት የሚወጡ ድምጾች እንዲሁም ከኃይማኖታዊ ተቋማት የሚወጡ ከልክ በላይ ድምጾች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በተለይ ከኃይማኖት ተቋማት በሚለቀቁ እና በኃይማኖት ተቋማት ስም በየመንገዱ የሚሰሙ ድምጾችን ከወዲሁ በጋራ ለመከላከል በውይይት መፍታት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በኃይማኖት ተቋማት የሚከሰቱትን የድምፅ ብክለት ለመቀነስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመጠቀም አማራጭ መኖሩም አመልክተዋል።

አቶ ዲዳ ከተማዋ የአፍሪካ መዲና ከመሆና በተጨማሪ ከ150 በላይ ኤምባሲዎች፣ 600 በላይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም 67 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኙባት ከተማ እንደመሆኗ ለነዋሪዎቿ ንጹህ እና ጤናማ አካባቢን መፍጠር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ባለሥልጣኑም በዚህ መነሻ መሠረት በከተማው የድምጽ ብክለት የሚያደርሱ ተቋማት ላይ የተለያዩ የክትትል እና ርምጃዎችን ይወስዳል ብለዋል።

በዘንድሮው በበጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ በተሠራ የአካባቢ ብክለት በሚያደርሱ ክትትል ከተደረገባቸው ተቋማት ውስጥ በአንድ ሺህ 221 ተቋማት ላይ ርምጃ እንደተወሰደ አቶ ዲዳ አስታውቀዋል።

ብስጭት፣ እንቅልፍ ማጣጥ፣ ራስ ምታት፣ ጭንቀትና አለመረጋጋት በከተማዋ የድምጽ ብክለት ጋር በተያያዘ በዋነኝነት የሚስተዋሉ አሉታዊ የጤና ችግሮች መሆናቸውን ጠቁመው፤ የድምጽ በክለት የሥነልቦና እና የአእምሮ ችግሮችን መከሰት ወይም ማባበስ እና ጆሮን የመስማት ሁኔታ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሊያናጋ ይችላል ብለዋል።

ችግሩንም ለመቀነስ በጉዳዩ ላይ በቀጣይነት ችግር ፈቺ ጥናት የማካሄድ፣ማህበረሰቡን ማስተማር፣ የወጡ ሕጎች መተግበር እና ከፍተኛ የድምጽ ብክለት ምንጮችን በመደበኛነት መከታተልና መቆጣጠር ሥራን ከባለድርሻ አካላት ጋር እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

በመድረኩ ላይ የአዲስ አበባ የኃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ዋና ጸሐፊ መጋቢ ታምራት አበጋዝ እንደገለጹት፤ አብሮነትና ወንድማችነትን ሊሸረሽሩ የሚችሉ ችግሮችን ከኃይማኖት አባቶች ጋር በውይይት መፍታት ተገቢ ነው።

በመሆኑም በኃይማኖት ተቋማት እና በኃይማኖት ተቋማት ስም የሚፈጠሩ የድምጽ ብክለቶችን በጥናት በመለየት ችግሮቹን በጋራ መፍታት ተገቢ ነው። ለማህበረሰቡም በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በጋራ ችግሩን መፍታትና መከላከል ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መልካም የገና በዓል!

የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በየዓመቱ በደማቅ ሁኔታ ከሚያከብሯቸው በዓላት አንዱ ገና ነው:: የገና በዓል በየዓመቱ ታህሳስ 29 እንደ ዘንድሮ ደግሞ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ታህሳስ 28 ይከበራል:: የገና በዓል መለያየት የጠፋበት፣ መከፋፈል የተወገደበት፣ የአንድነት እና የሰላም በዓል ነው።

የገና በዓል የአብሮነት በዓል ነው:: በልደት በዓል ሰውና አምላክ፣ እንስሳትና ሰው፣ እረኛና ንጉሥ፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ሕጻንና አረጋዊ፣ በአንድ በረት ተገናኝተዋል። እነዚህ ሁሉ በበረት ውስጥ ሲገናኙ አብሮነትን ፈልገው ነው:: ከመለያየት ይልቅ አንድነትን ሽተው ነው:: ለዛሬዋም ኢትዮጵያ የሚያስፈልገው ይኸው አብሮነት ነው::

የጾታ፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የቋንቋ፣ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት፣ ልዩነቶች ተፈጥሯዊ ናቸው:: ሆኖም እነዚህ ልዩነቶች የቅራኔና አለመግባባት ምንጮች ሊሆኑ አይገባም:: ኢትዮጵውያን በልዩነቶች ውስጥ በአንድነት ደምቀው የሚታዩባትና ህብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት ጎልቶ የሚታይባት ሀገር ናት::

እነዚህን ልዩነቶች እንደጌጥ በመቁጠር ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ ማማ መውሰድ ይገባል:: በገና ዕለት በበረቱ ውስጥ የተወለደውን ህጻን በመመልከት ዘርና ቋንቋ እንዲሁም ጾታ ሳይለያቸው የተለያዩ ሰዎች በአንድነት እንደተሰባሰቡ ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያውያን አንድታቸውን ማጽናት ይጠበቅባቸዋል::

የገና በዓል አንዱ መሠረት ሰላም ነው:: በጌታ ኢየሱስ ልደት ለዓለም ሁሉ የሚሆን ዘላለማዊ ሰላም ተገኝቷል። ይህም “ክብር እግዚአብሔር በሰማያት ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ” እያሉ ቅዱሳን መላእክት በመዘመራቸው ተረጋግጧል። ሉቃ 2፥14። ስለዚህ በክርስቶስ ያገኘነው እውነተኛ ሰላም በእኛ ጸንቶ እንዲኖር ዘወትር በጾምና በጸሎት እየተጋን ስለሰላም የምንማፀን ሆነን ልንገኝ ይገባል። ሰላም የክርስትና መታወቂያ ዓርማ ነውና።

ስለዚህም እኛ ኢትዮጵያውያን ገናን ስናከብር ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ሰላማችንን በማረጋገጥ ሊሆን ይገባል:: በሰላም እጦት የታመመችው ሀገራችን ወደ ቀድሞ ሰላሟ እንድትመለስና ሁሉም ያለስጋት ወጥቶ የሚገባባት ፤ ነግዶ የሚያተርፍባት እና ሮጦ የሚያሸንፍባት የሰላም ሀገር እንድትሆን የበኩላችንን አስተዋጽኦ ልናበረክት ይገባል:: ይህ ሲሆን የገና በዓል ኃይማኖታዊ እሴቱን የተላበሰ ይሆናል፡፤

የገና በዓል የተስፋና የብርሃን በዓል ነው:: ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል በዲያብሎስ ቁራኝነት ተይዞ የነበረው አዳም ወደሚደነቀው ብርሃን የተሸጋገረው በክርስቶስ ልደት ነው። እናም በልደቱ የተገኘነውን የጽድቅ ብርሃን ጠብቀን ለመኖር አንዳችን ለአንዳችን ተስፋና ብርሃን መሆን አለብን:: ወንድም ወንድሙን ከመግደልና ከማሳደድ ወጥቶ አለኝታው ሊሆን ይገባል:: እኛ ኢትዮጵያውያን የትኛውንም ሃይማኖት እንከተል፤ የየትኛውም ብሔር አባል እንሁን ከልዩነታችን ይልቅ አንድነታችን የሚያይል፤ ከችግራችን ይልቅ ጥንካሬያችን የሚልቅ፤ ከመከራችን ይልቅ ተስፋችን የሚበዛ እና እጣ ፋንታችን የተሳሰረ በመሆኑ አንዳችን ለሌላችን መከታ ፤አንዳችን ለሌላችን ተስፋ ልንሆን ይገባል:: ይህ ሲሆን የገና በዓልን ሙሉ በረከት የሚገኝ ይሆናል::

በክርስትና አማኞች የገና በዓል የይቅርታ በዓል ነው:: በአዳም በደል ምክንያት ከአብራኩ የተከፈሉ በሙሉ በደለኛ ሆነው የነበሩበትን ዘመን ለውጦ አዳምንና የልጅ ልጆቹን በደል ደምስሶ ፍቅርን ይመሰርት ዘንድ ጌታ ተወለደ። በምድርና በሰማይ ላሉት ፍቅርን መሠረተ። እርሱ የሰው ልጆችን በደል ሳይቆጥር ሁሉን ይቅር እንዳለ ክርስቲያንም የበደሉትን ሁሉ ይቅር ይል ዘንድ የፈጣሪው ትዕዛዝ ነውና ዘወትር ሊፈጸም የሚገባው ትዕዛዝ ነው:: የዛሬዋም ኢትዮጵያ ይህ መለኮታዊ ትእዛዝ ያስፈልጋታል::

ዛሬ ኢትዮጵያውያን በረባው ባልረባው የምንጋጭ፤ ጦር የምንማዘዝ እና ቂም ቁርሾ የምንቋጥር ሆነናል:: በዚህም በርካቶች ከቀያቸውና ከቤታቸው እንዲሰሰዱ፤ እንዲፈናቀሉና አልፎ ተርፎም አካላቸውን ህይወታቸውን እንዲያጡ ሆነዋል::ይህ ድርጊት እንዲያበቃ የገና በዓልን ምሳሌ በማድረግ ኢትዮጵያውያን ልባቸውን ለይቅርታ ሊያዘጋጁ ይገባል::

የገና በዓልን ስናከብርም ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በየመጠለያ ጣቢያው የሚያሳልፉትን ሰዎች በማሰብ ሊሆን ይገባል:: የእነዚህ ሰዎች ስቃይ እንዲበቃና ዳግም በኢትዮጵያ ግጭት፤ ጦርነት፤ ስደትና መፈናቀል እንዲቆም ኢትዮጵያውያን ልባቸውንን ለይቅርታ ክፍት ሊያደርጉ ይገባል::

ዛሬ ላይ የገና በዓልን ስናከብር በልደቱ ያገኘነውን ሰላም፣ ነጻነት፣ ይቅርታ፣ ብርሃንና ፍቅር ዋጋ የተከፈለበት ጸጋ የወረስንበት መሆኑን በማመንና በዕለት ተዕለት ሕይወታችንም ለመተግበር በመጣጣር ሊሆን ይገባል:: መልካም የገና በአል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ውልደቱን ስናስብ

ቴልጌልቴልፌልሶር (ኩሻዊው ባለዘውድ)

ከኢየሱስ ክርስቶስ የመወለድ ዓላማው ጋር ከሚጣጣሙ መልካም ቃሎች መካከል ‹ፍቅር ተወለደ› የሚለው ሁነኛ ገላጭ ቃል ይመስለኛል:: እንዴትም ብናስብ ልደትና ትንሳኤውን ከዚህ ለይተን ማየት አንችልም:: ግን ኢየሱስ ለምን ተወለደ? ለዛውም በከብቶች በረት. . ?::

ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው በሰው ልጆች ፍቅር አስገዳጅነት ነው:: ይህም ማለት ሞትን በፍቅር ሊሽር፣ ጥላቻን በእርቅ፣ መለያየትን በወንድማማችነት ሊቀይር ነው:: እናንተ በፈጣሪ አምሳል የተፈጠራችሁ የክርስቶስ ቤተ መቅደሶች እንጂ በዘርና በጥላቻ መንፈስ ተፈጥሮአዊ ቤተመቅደሳችሁን እንድታረክሱ አይደለም ሊለን ነው::

ደም አታፍሱ ፣ በመለያየትና በመራራቅ ተፈጥሮአዊ ማንነታችሁን አታቆሽሹ ሊለን ነው:: እንደ አንድ አማኝ ክርስቲያን ይሄ እውነት በብዙዎቻችን ዘንድ የታመነ እውነት ሆኖ በልባችን ውስጥ እንዳለ ይሰማኛል ::

በእየሱስ መወለድ በኩል ለሰው ልጅ ሁሉ ሰላም ሆኗል:: ዳግም እንዳንጣላ፣ ዳግመኛ እንዳንከድ፣ በወንድማማቾች መካከል ጠብና መገፋፋት እንዳይኖር በልደቱ መስክሮ በትንሳኤው አረጋግጦልናል:: አማኝ ነን የምንል ሁሉ ከዚህ የሥርዓት አውድ ስር ሆነን ስለሌሎች የምናስብበት ጊዜ ሊሆን ይገባል::

አሁን ባለው የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ የኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚች ምድር መምጣት ዋጋ ያለው ሲሆን አይታይም:: በአማኝነቱ የሚታወቀው ሕዝብ በፈጣሪ ፊት ነውር የሆነን ድርጊት በመፈጸም የልደቱን ትርጉም እየሳተ ይገኛል::

እግዚአብሄርን የሚያውቁ ልቦች የመጀመሪያ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ፍቅር ነው:: ይሄን እውነታ ታላቁ መጽሀፍ ቅዱስ በቆሮንቶስ መልዕክቱ ‹እግዚአብሄር ፍቅር ነው፣ ፍቅር የሌለው እግዚአብሄርን አያውቅም፣ እግዚአብሄር ፍቅር ነውና› ሲል ይነግረናል::

ፍቅር በሆነ አምላክ፣ ፍቅር በሆነ ሃሳብና ጥበብ ሰው ሆነናል ታዲያ ጥላቻችን፣ መለያየታችን ከየት መጣ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ልደቱን ካለማወቅ እና ከልደቱ በኋላ ያለውን የምድር ላይ የሰላሳ ሶስት ዓመት የፍቅር ስብከት ካለመረዳትና ብሎም በመስቀል ላይ የዋለልንን ውለታ ከመዘንጋት የመጣ ነው::

እንደእውነቱ ከሆነ መቼም ከፍለን በማንጨርሰው የፈጣሪ ውለታ ውስጥ ነን:: ውለታው በፍቅርና በይቅርታ፣ በትህትናና በወንድማማችነት የሚከፈል እንደሆነ ቢገባንም ይህን ለማድረግ ስንበረታ ግን አንታይም:: ሌሎችን በማሳደድ፣ ለሌሎች ውድቀት መንስኤ በመሆንና በእርስ በርስ መገፋፋት ውስጥ ማንም በማይችለው መጨካከን ውስጥ ነን:: ታዲያ በዚህ ከፈጣሪ በራቀ ሰውነት እንዴት ነው ውለታውን የምንከፍለው?።

ሉዓላዊነቱን ትቶ ክብር ለሰጠን ጌታ፣ ሰው አምላክ አምላክ ሰው በሆነ ጥበብ ከዝቅታችን ከፍ ላደረገን አምላክ ሌላ የምንሰጠው ባይኖር እንዴት መዋደድ ያቅተናል:: እኛ እኮ ወንድማማቾች ነን.. ብዙ ታሪክ ያጋመደን፣ እልፍ ሥርዓት ያስተሳሰረን የባህልና የወግ ድብልቆች ስለምን ፍቅር የሌለው ልብን መረጥን? የልደቱ ሚስጢር ይሄ ነው:: ፍቅር ከሌለን እግዚአብሄርን አናውቀውም:: በየዓመቱ ፍቅር ተወለደ ብለን ቤታችንን በአበባና በውዳሴ አሸሞንሙነን ብናከብረው ትርጉም የለውም::

ሌላው በጌታ መወለድ ቀን ልናውቀው የሚገባን ታላቁ ቁም ነገር የክብር ስፍራን ትቶ በከብቶች በረት የመወለዱን ሚስጢር ነው:: ታላቁ ጌታ ቤተመንግሥትንና ታላላቅ የክብር ቦታዎች ሲገቡት የማይረባውንና በዝቅታ የተሞላውን የከብቶች በረት መርጧል:: በመኳንቶችና በመሳፍንቶች በብዙ አጋፋሪዎች ፊት ምናልባትም በታላላቅ አዋጆች በኩል ሊወለድ ይችል ነበር::

እርሱ ግን ያን አላደረገም:: በዳዊት ከተማ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ በመጡ እንግዶች በተሞላ ቤት ውስጥ ማረፊያ አልነበረም:: በሃይሉ ሁሉንም ማድረግ እየቻለ ሃይል እንደሌለው ሆነ:: በመጨረሻም በከብቶች በረት በእንስሳቶች መሀል ተወለደ:: ለምን ስንል የምናገኘው መልስ ትህትና የሚለውን ነው::

የፈጣሪ ተቀዳሚ ባህሪ ከሆኑ ቀዳማይ እውነቶች ውስጥ አንዱ ትህትና ነው:: በጸሎተ ሀሙስ እለት የደቀመዛሙርቱን እግር ሲያጥብ፣ በሆሳዕና ቀን በአህያ ውርንጭላ ተሳፍሮ ሲሄድ እናውቃለን:: ይሄ ሁሉ ትህትናን ሊነግረንና ሊያስተምረን ነው:: ሰው ከፍቅርና ከትህትና ጋር እስካልቆመ ድረስ ምንም እንደሆነ ሊነግረን በታላቅ ጌትነቱ ውስጥ ዝቅታን መርጦ ተወለደ::

> **በአጭሩ የገና በዓል የሞተልንን ጌታ በግብር፣ በሃሳብ የምንመስልበት የእርቅና የተሀድሶ በዓል ነው:: በአንድነትና በፍቅር በይቅርታም የምንተቃቀፍበት የይቅር ለእግዜር ሰሞን ነው**

እኛ የእሱ የእጅ ሥራዎች ነን:: አምሳሉ ነው ሰው ያረገን:: ሃሳቡ ነው የፈጠረን:: አባታችን በጌትነት ትህትናን ከመረጠ እኛ የማንረባው ልጆቹ ስለምን በመገፋፋትና በጥላቻ ቆምን? ገና ወይም የጌታ መወለድ አሁን ባለው የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ሊገለጥ የሚገባው እንዲህ ባለው ጥያቄና መልስ ውስጥ ነው:: ፍቅር ተወለደ ብለን ስንናገር ዝም ብሎ መሆን የለበትም:: የመወለዱን ዓላማ ወደሕይወታችን አስገብተን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም በመኖር መግለጥ አለብን::

ዓለምን ለመፍጠር ከተጠበበው ጥበብ ሁሉ እኛን ለማዳን የተጠበበው ጥበብ እንደሚልቅ የኃይማኖት ሊቃውንቶች ይናገራሉ:: የዓለም አፈጣጠር በራሱ ከሰው የማሰብ እና የመረዳት አቅም በላይ የሆነ ነገር ነው:: እኛን ለማዳን የተጠበበው ጥበብ ከዚህ እውነት ሲልቅ የተከፈለልን መስዋዕት ምን ያክል እንደሆነ ማሰቡ አይከብድም::

ለሞተልን ደግሞም ሞትን አሸንፎ በአብ ቀኝ ላለው ጌታ የተመቸን ልንሆን ይገባል:: ደም እያፈሰስን፣ ከወንድሞቻችን ጋር ሆድና ጀርባ ሆነን ገናን ብናከብረው፣ ትንሳኤውን ብንዘክረው ትርጉም የለውም::

በአጭሩ የገና በዓል የሞተልንን ጌታ በግብር፣ በሃሳብ የምንመስልበት የእርቅና የተሀድሶ በዓል ነው:: በአንድነትና በፍቅር በይቅርታም የምንተቃቀፍበት የይቅር ለእግዜር ሰሞን ነው:: በአጠቃላይ ከቂም የምንሽርበት፣ ከጥላቻ የምንጸዳበት በአዲስ መንፈስ ወደ ነገ የምናገድምበት የመሻገር በዓላችን ነው::

# በመቅደላ ጦርነት ወቅት የተዘረፉ ከ10 በላይ ጽላቶችን ለማስመለስ ጥረት እየተደረገ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመቅደላ ጦርነት ወቅት በእንግሊዝ ጦር የተዘረፉ ከ10 በላይ ጽላቶችን ለማስመለስ ጥረት እያደረገ መሆኑን የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ። የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ፀጉር እና በመቅደላ ጦርነት ወቅት በእንግሊዝ ጦር የተዘረፉ ታሪካዊ ቅርሶች ትናንት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል።

የተመለሱት ታሪካዊ ቅርሶች በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈሪ መለሰ ቅርሶቹን ይዘው በመምጣት ለኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው አስረክበዋል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በተለያዩ ምክንያቶች የሀገሪቱ ቅርሶች ከሀገር ወጥተዋል። ከወጡትም ትልቁን ድርሻ የሚወስደው በ1861 ዓ.ም እንግሊዝ ጦር ከመቅደላ የተዘረፈው ነው። በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ ቅርሶችን በአንድ ቤተ መጻሕፍት በማደራጀታቸው የእንግሊዝ ጦር ቅርሶቹን በቀላሉ እንዲወስድ እድል ፈጥሯል።

የተወሰዱትን ቅርሶች ለማስመለስ ከአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ በዚህም በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች ተመልሰዋል። አሁን ደግሞ የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ፀጉር እና ከመቅደላ የተዘረፉት ሁለት በብር የተለበጡ ዋንጫዎች፣ አንድ የቀንድ ዋንጫ፣ ደብዳቤዎች እንዲሁም አንድ ጋሻ ማስመለስ ተችሏል ብለዋል።

ዶክተር ጃኮቦ ግንሺ የሚባሉ እንግሊዛዊ ከኢትዮጵያ የተወሰደውን ጽላት ገዝተው ቤታቸው አስቀምጠውት ነበር። ከሳቸው ጋር በመነጋገር ታቦቱ በቤተ ክህነት በኩል ወደ ሀገር እንዲመለስ መደረጉን



ፎቶ ፡ ዳኜ አበራ

አውስተዋል።

በቀጣይ በመቅደላ ጦርነት ወቅት በእንግሊዝ ጦር የተዘረፉ ከ10 በላይ ጽላትን እና ሌሎች ቅርሶችን ለማስመለስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቅርስ አስመላሽ ኮሚቴ አባል ዶክተር አሉላ ፓንክረስት የኢትዮጵያን ቅርሶች በማስመለስ ትልቅ ሚና እንዳበረከቱ ተናግረዋል።

በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈሪ መለሰ በበኩላቸው፤ ከ130 ዓመት በፊት ከኢትዮጵያ መቅደላ በእንግሊዞች ተዘርፈው ከነበሩት ከሁለት ሺህ በላይ ቅርሶች መካከል በሁለተኛ ዙር የመጡ ቅርሶች ናቸው። በመጀመሪያው ዙር 19 የሚደርሱ ታሪካዊ ቅርሶችን ከእንግሊዝ ሀገር በማምጣት ለኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ማስረከብ ተችሏል። በቅርሶቹም ላይ ከመቅደላ የተወሰዱ እንደሆነ የሚገልጽ ጽሑፍ እንዳለበት ጠቁመዋል።

ቅርሶቹን በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቅርስ አስመላሽ ኮሚቴ እና ሼኽራዛድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ባለፈው መስከረም ወር ማስመለሳቸውን ገልጸው፤ መንግሥት ከሀገራችን ተዘርፈው በተለያዩ ሀገራት ሙዚየም የሚገኙ ቅርሶችን ለማስመለስ የሚያደርገውን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ እና እንግሊዝ መካከል በተካሄደው ጦርነት ወቅት የእንግሊዝ ጦር ከኢትዮጵያ ውድ ብራናዎችን፣ አክሊሎች፣ መስቀሎችን፣ የወርቅ ዋንጫዎችን፣ የንጉሣውያንና የቤተክርስትያን ቁሳቁሶችን ጋሻና የመሳሰሉትን መዝረፉቸው በታሪክ መዛግብት ተጠቅሶ ይገኛል።

በመቅደላ ጦርነት ወቅት የንጉሡ የሰባት ዓመት ልጅ ልዑል አለማየሁ ወደ እንግሊዝ ተወስዶ በዚያው እንዳረፈ የሚታወቅ ሲሆን የልዑል አለማየሁ ጸጉር እና የሳቸው ሞግዚት የካብቴን ስፒዲ ጸጉር እንደቅርስ ባይቆጠርም ከእንግሊዝ ይልቅ በኢትዮጵያ መቀመጡ ትልቅ ዋጋ እንደሚኖረው ረዳት ፕሮፌሰር አበባው ተናግረዋል።

## ስምምነቱን ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በመደገፍ አጋርነታቸውን ሊያሳዩ እንደሚገባ አመልክተዋል።

ስምምነቱ ለቀጣናው ችግር ይዞ ይመጣል ብለው የሚያስቡ አካላት ቆም ብለው ማሰብ አለባቸው ያሉት ዶክተር በርከድ፤ ኢትዮጵያ በሶማሊያና በተለያዩ ሀገራት የሰላም ማስከበር ሥራ በብቃት እያከናወነች የምትገኝ ሀገር መሆኗን ከግምት ውስጥ ማስገባትና ትብብሩ ለተሻለ ተጠቃሚነት የተፈጸመ መሆኑን መገንዘብ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በጂቡቲና በአካባቢው በርካታ ሀገራት የጦር ቤዝ በማቋቋም የባህር ላይ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ አስታውሰው፤ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በውል ላይ በተመሠረተ አካሄድ በአካባቢው ለመሥራት የጀመረችው ጥረት የተለየ ተቃውሞ ሊገጥመው አይገባም ሲሉ ጠቁመዋል።

በስምምነቱ ዙሪያ በሶማሌ ላንድ የሚገኙ ዜጎችም ሆኑ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከፍተኛ ደስታ ተሰምቷቸዋል፤ ለስምምነቱ ተፈጻሚነትም በትኩረት እንሠራለን ብለዋል።

ኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ ግንኙነት እ.አ.አ. ከ1996 ጀምሮ እንዳላቸው ያስታወሱት ዶክተር በርከድ፣ አሁን ላይ የተፈረመው ስምምነት ደግሞ በባህር ሃይል፣ በንግድና ኢኮኖሚ እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን በማሳደግ ለቀጣናው ተጠቃሚነት ጉልህ ፋይዳ ይኖረዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በ20 ኪሎ ሜትሩ የባህር በር የሚኖራት የማሪታይም እንቅስቃሴ በአካባቢው ያለውን የባህር ላይ ወንጀል በመከላከልና የኢኮኖሚ ትብብርን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

ሶማሊ ላንድ ከኢትዮጵያ ጋር የደረሰችውን ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ታደርጋለች፤ ይህ ስምምነት ቀጣይነት እንዲኖረውና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነቱ እንዲዳብር እንሠራለን ብለዋል።

"እኛ የታላቋ ሶማሊያ አስተሳሰብ አራማጅ አይደለንም። እንደ ሶማሊ ላንድ ከአካባቢው ጋር በትብብር መሥራትን ምርጫችን አድርገን እየተንቀሳቀስን ይገኛል" ሲሉ ተናግረዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሶማሊላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ መካከል የተፈረመው የትብብርና የአጋርነት መግባቢያ ሰነድ ኢትዮጵያን የበርበራ ኮሪደርን በስፋት እንድትጠቀም የሚያስችል መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

## ምዕመናን በዓሉን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የልደት በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ ምዕመናን በተለመደው የመተጋገዝ ቅዱስ ባህል መሠረት እርስ በእርስ በመረዳዳት በዓሉን ሊያከብሩ ይገባል ብለዋል።

በሀገሪቱ በተከሠተው ድርቅና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ድጋፍ የሚሹ ወገኖች በርካታ መሆናቸውን ገልጸው፤ የወገን ደራሽ ወገን ነውና ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳትና በመደገፍ በዓሉን ሊያከብሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በሀገሪቱ የሚስተዋሉት ግጭቶች፣ መለያየት፣ መጨካከን እና ለእኔ ለእኔ መባባሉ ያመጣልን ነገር ቢኖር ሁለንተናዊ ውድመት ብቻ ነው ያሉት አቡነ ማትያስ፤ ግጭቶችና አለመግባባቶች ተወግደው ሰላም እንዲሰፍንና ሀገራዊ አንድነት እንዲረጋገጥ መሥራት ይገባል ብለዋል።

ችግርን በምክክርና በይቅርታ መፍታት አማራጭ የሌለው ጥበብ መሆኑን ገልጸው፤ የሃይማኖት መሪዎች፤ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ መንግሥትና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተግተን ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

ሰው ችግሩን በልቡ እያወቀና በዓይኑ እያየ እንዴት ገደል ውስጥ ይገባል?፣ ዕርቅና ይቅርታ ማንን ጐዳ?፣ ሰላምና አንድነት ማንን አከሰረ?፣ ሰበብ አስባብ እየተፈለገ በሆነውም ባልሆነውም ከመተላለቅ ይልቅ ኢትዮጵያ የሁላችን ናት ብለን በእኩልነትና በስምምነት ልንኖር ይገባል ሲሉ አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል በበኩላቸው፤ ምዕመናን የክርስቶስን ልደት ሲያከብሩ ከራስ ወዳድነትና ከመገፋፋት መንፈስ በመራቅ፣ በመላ ሀገሪቱ ሰላምን በማስፈን፣ የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት፣ ተፈናቃዮችን ወደቀድሞ መኖሪያቸው በመመለስ እና ያዘኑትን በማጽናናት መሆን አለበት ብለዋል።

ለታመሙት ምህረትን፣ ለደከሙት ብርታትን፣ ለታሰሩት ይቅርታን፣ ላዘኑት መጽናናትን፣ በጭንቀትና በመከራ ላይ ለሚገኙት ሰላምና ፍቅሩን እንዲሰጣቸው ምዕመኑ በጸሎት እንዲተጋ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ በበኩላቸው፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ሲያከብር በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያት ከቤታቸው የተፈናቀሉና በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

የሰላም ልዑል በተወለደባት ዕለት ሀገሪቱን እየፈተናት ያለውን የሰላም እጦት አስወግዶ መጪውን ትውልድ ለመታደግ መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ ባስተላለፉት የበዓል መልዕክታቸውም፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስን ልደት በዓል ሲያከብር የተለያየ ችግር የደረሰባቸውን ወገኖች በተለይም ተንከባካቢና አሳዳጊ የሌላቸውን ህጻናት፣ አቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ህሙማንን፣ በድህነት የሚማቅቁና ተፈናቅለው የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

የክርስቶስ ልደት በዓል የሚያስተምረው መሠረታዊ ቁም ነገር እርቅና ሰላምን ተግቶ መፈለግን ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ምዕመናኑ የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በተለይም ሀገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን እጅግ በተጠማችበት ወቅት ልዩነትንና ክፉ ውጤትን ለማስቀረት ዋጋን በመክፈል ሊሆን ይገባል ብለዋል። ለበዓሉ አከባበር ከሚሰጠው ዋጋ ሰላምና አንድነት እጅጉን የላቀ መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል።

## "የክርስቶስን ልደት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በኦሪትና በነቢያት ክርስቶስ ይመጣል የሚለውን ቃል የሰሙና ያነበቡ ብዙዎች ነበሩ። የጠበቁት ግን በነገሥታት ቤተ መንግሥትና በባለጸጎች እልፍኝ ውስጥ ነበር። የዓለምንና የሰው ልጅን ታሪክ የቀየረው ክርስቶስ በበረት ውስጥ ይወለዳል ብሎ የጠበቀ አልነበረም። በዚህም የተነሣ የዓለም ታሪክ በአስደናቂ ሁኔታ ሲቀየር ዓለም ራሷ ግን ተኝታ ነበር ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤

የዓለምንና የሀገርን ታሪክ የሚቀይሩ ነገሮች በተለመዱና በሚጠበቁ መንገዶች ላይመጡ ይችላሉ። እንዲህ ባለ ሁኔታ መረዳት የሚገኘው እኛ የማናውቀው፣ ያልደረስንበትና የማንገምተው ሌላም መንገድ ሊኖር እንደሚችል ለመቀበል ከተዘጋጀን ብቻ ነው ብለዋል።

ነገሮች ሁሉ እኛ በምናውቀው፣ በምንገምተውና በለመድነው መንገድ ብቻ እንዲመጡ ከጠበቅን ሊያልፉን እንደሚችሉ ገልጸው፤ የቤተ ልሔም ከተማና የይሁዳ አውራጃ ሰዎች የዓለምን ታሪክ ከቀየረው ከክርስቶስ ልደት ሳይሳተፉ የቀሩት ከለመዱትና ከሚያውቁት ውጭ ለሚመጣ ነገር ዝግጁዎች ስላልነበሩ መሆኑን አመልክተዋል።

የዓለምን ታሪክ የቀየረው ክርስቶስ በእንግዶች ማደሪያ ሥፍራ ስላላገኘ የመጣው ወደ በረት ነው። ያልተጠበቁት ሰብአ ሰገል ባልተጠበቀ ቦታ በበረት ተገኙ። ካልተለመደ ሥፍራ፣ ባልተለመደ መንገድ ተጉዘው፣ ያልተጠበቀ ቦታ ተገኙና ያልጠበቁትን ተአምር አዩ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሀገርን ምንጊዜም የሰው ልጅ ሲጓዝባቸው በኖሩ መንገዶች ብቻ መታደግ እንደማይቻል በመልዕክታቸው አስተላልፈዋል።

ሰው ሁሉ በሚያውቃቸው፣ በለመዳቸውና በተረዳባቸው መፍትሔዎች ብቻ ሀገርን መመንጠቅ አይቻልም። መኪኖችና አውሮፕላኖች በሚጓዙበት መንገድ መንኮራኩሮችን ወደ ሕዋ መውሰድ እንደማይቻለው ሁሉ። ወደ ሕዋ ለመሄድ የምድር ስበትን ሰብሮ፣ በፍጥነትና በኃይል ባልተለመደ የጉዞ ስልት መመንጠቅን እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ እንዲህ ያለ ጉዞ ከተለመደውና ከሚታሰበው መንገድ ወጥቶ መሄድን የግድ ይላል። ስለዚህም ይሄንን መንገድ የሚረዳ ከሚጠበቀውና ከሚታሰበው ውጭ ለመጓዝ ፈቃደኛ የሆነ ወገንን ይፈልጋል። አሁን ሀገራችን ያለችው እንዲህ ባለ ጉዞ ላይ ነው ብለዋል።

በተለመደ እሽክርክሪት ነባር ችግሮችን ፈትቶ አዲስ ውጤት ማስመዝገብ አይቻልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የተለየ፣ ያልተጠበቀ፣ ከምናውቀው የወጣና ያልታሰበ መንገድ ይፈልጋል። በርግጥ እንዲህ ያለው መፍትሔ በተለመደው መንገድ ለሚያስቡና ለሚጓዙ እንግዳና የሚረብሽ እንደሚሆን እሙን መሆኑን ገልጸዋል።

በተለመደው መንገድ የተለመደውን የሚከውኑ ወገኖች ቢገርማቸውም፤ ባልተለመደው መንገድ የሚመጣው እንግዳው መፍትሔ ግን፣ ታሪክን ላይመለስ መቀየሩ አይቀሬ ነገር መሆኑን ገልጸው፤ መጀመሪያ የሚቀበሉት ጥቂቶች ቢሆኑም እየቆዩ ግን ብዙዎች እየተረዱትና እየተቀበሉት መሄዳቸው ርግጥ መሆኑን አመልክተዋል።

የክርስቶስን ልደት ስናከብር በልደቱ ካገኘነው በረከትና መዳን ቀጥለን ዓለም የተቀየረበትን መንገድ ማጤንና እኛም የምንሄድበትን መንገድ መገምገም አለብን ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ከገና ባሻገር

ገና ወይም በዓለ ልደት አልያም ብርሀነ ልደት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየዓመቱ ታኅሣሥ 29፣ በየአራት ዓመቱ ደግሞ ታኅሣሥ 28 ቀን የሚከበር ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓል ነው። ገና እየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዘር ሁሉ ለማዳን ከሰማይ ሰማያት ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማሪያም በበጎች ግርግም የተወለደበት ልደት የሚዘከርበት ዕለት ነው። ለዚህ ነው የበዓላት ሁሉ በዓል ተደርጎ የሚወሰደው። የገና ስረወ_ ቃል (መነሻ) የበዓሉ ሁሉ ንጉሥ ፣ ታላቅና ገናናነት ከሚገልጸው "ገናና" ከሚለው ቃል የሚመዘዝ ነው። እየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ ቤተልሔም ሲወለድ ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ከእነ ሔሮድስ ተሰውሮ ለእረኞች ተገልጧል።

እረኞችም ከመልዓክት ጋር "ስብሀት ለእግዚአብሔር በሰማያት ..." ሲሉ ለክብሩ ዘምረዋል። አዋቂዎቹ ሰብዓ ሰገሎች የከበረ ስጦታ ይዘው በቤተመንግሥት ሲፈልጉት በበጎች ግርግም ነበር የተገኘው። እነዚህ ተምሳሌቶች እየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ መካከል ቆሞ የነበረውን የጥል ግድግዳ ለማፍረስ፤ እርቅን ሰላምን ለማውረድ መምጣቱን ያበስራል። ገናን ለ2015 ዓመታት ጊዜ ስናከብረው ፍቅሩንና ሰላሙን ልብ አላልነውም። አልኖርነውም። ገናን ከቅርጫው ከዳቦው፣ ከድግሱና ሸቀጥ ከመሰጣጣት ባሻገር የልደቱን አብይ አላማ አልኖርነውም። በተለይ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በሀገራችን የተከሰተው ቀውስ፣ ጭፍጨፋና የመረረ ጥላቻ ይሄን የሚያረጋግጥ ነው። እስኪ በብርሀነ ልደቱ መስኮት የሌሎችን ባህላዊ ወረቶቻችን cultural capital አኳኋንና አከራረም እንቃኝ።

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚከበሩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሁነቶች የተሸከሙትን ግዙፍ መልዕክቶችና አንድምታዎች አለፍ አለፍ ብለን እየተመለከትን ሂሳብ እናወራርድ። ፍቼ ጨምበለላ፣ ቡሔ ፣ ሻደይ ፣ አሸንዳ፣ ሶለል አይነ ዋሬ ፣ እንቁጣጣሽ ፣ መስቀል ፣ መስቀላዮ፣ አጋመ፣ ጊፋታ፣ ኢሬቻን ፣ ጋሮ፣ ቺሜሪ፣ ትንሳኤ፣ ወዘተ... በአንድም በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገራችን ማኅበረሰቦች የሚከበሩ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ናቸው። ሁሉም ማለት ይቻላል ተስፋን ፣ ፍቅርን፣ ነፃነትን ፣ አብሮነትን ፣ አንድነትን ፣ ምስጋናን ፣ እርቅን ፣ ይቅርታን፣ እኩልነትን ፣ ወዘተረፈ.... የሚያውጁ፣ የሚለፍፉና የሚሰብኩ ናቸው።

ግን በነቂስ ወጥተን ለዘመናት በየዓመቱ በአደባባይ የምናከብራቸው የምንዘክራቸውን ያህል በዕለት ተዕለት ኑሮአችን አንኖራቸውም። አንለማመዳቸውም፡፡ ይሁንና ከገጠሙን ቀውሶች ፣ ፈተናዎች መውጣት ማገገምና ማንሰራራት የቻልነው በቀሩን ሽርፍራፊ እንጥፍጣፊ በባህላዊ ንብረቶቻችን social capital መሆኑን ልብ ይላል። ባለፉት 27/50 ዓመታት ቀን ከሌት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ እንደ ተሰበከው ልዩነት ፣ ጥላቻና ዘርኝነት ቢሆን ኑሮ እርስ በእርስ ተበላልተናል። ተጨራርሰናል። ለዚህ ነው መዳኛችን ፣ ማገገሚያችንና ማንሰራሪያችን የሆነውን ባህላዊ ወረት ወደ ሙላቱ መመለስ ለነገ የሚባል ጉዳይ የማይሆነው።

ባህላዊ ወረታችን ለበጎ አላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል። የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ለበቀል ተነስቶ የነበረውን የአርባ ምንጭና የአካባቢውን ወጣት ለምለም ሳር ይዘው ተንበርክከው

**ባልንጀራህን ፤ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚሉ አብርሃማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን ፤ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን !?**

በመለመን ቁጣውን አብርደው መልሰውታል። ይህን የሀገር ሽማግሌዎች ገድል በጥሞና ለተረዳው የአርባ ምንጬን እሳት ብቻ አይደለም ያጠፉት የአርባ ምንጬን ጥፋት ተከትሎ በመላ ሀገሪቱ ሊዛመት የነበረውን የበቀል ሰደድ እሳት ጭምር እንጂ። ቁጣ አብራጁ ይህ የጋሞ አባቶች ልመና (ጋሞ ወጋ) እየጠፋ ፣ ትኩረት እየተነፈገው ያለው ባህላዊ ወረታችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው።

የጋሞ አባቶች ከአራት ዓመት በፊት ልዩ የበጎ ሰው ተሸላሚ መሆናቸው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለ አንዳንች ልዩነት ዳር እስከዳር አድናቆትን ተቀባይነትን ያተረፈው በዚህ እሳቤ ነው። ሕግን ለማስከበር ከምናደርገው ጅምር ጥረት ባልተናነሰ በየአካባቢው እንደ ጋሞ ወጋ ዓይነት የሽምግልና ፣ የእርቅ ባህላዊ ካፒታሎቻችንን ላይም መሥራት ይጠበቅብናል። ከዚህ መሳ ለመሳ የአክራሪነት አዝማሚያ ፣ እኩይ አስተሳሰብ እንዲገታ ብሎም ተሸንፎ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ገለል፣ ዘወር እንዲል ድልብ የሆኑ የባህላዊ ንብረቶቻችን ወረቶች የማይተካ ሚና አላቸው።

ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህላዊ ወረቶች ባለፀጋ ስለሆኑ የየራሳቸውን መዋጮ ማበርከትና ወደ ሥራ መግባት ይጠበቅባቸዋል። በየአካባቢያችን፣ በየቀዬአችን የምናንፀው፣ የምናቀነቅነው ከባቢያዊ ብሔርተኝነት ወደ አክራሪነት፣ ፅንፈኝነት የሚያንደረድር ወደ ገደል አፋፍ የሚገፋ ስለሆነ እነዚህን ባህላዊ ወረቶች በመጠቀም መግታት ያስፈልጋል። የዜጎች ማንነት እሴት እንደተከበረ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያደርሰንን ቀና መንገድ በቅንነት መቀላቀል ፣ መያያዝ ይገባል።

ይህ ሀገራዊ ብሔርተኝነትም ከገደቡ ፣ ከውሃ ልኩ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ። አይደለም ዘውጌአዊ ፣ ወንዜአዊ ብሔርተኝነት ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በአግባቡ ካልተያዘ ፤ የጎረቤቱን የሚጎመጅ፣ የሚመኝ ፣ የሚመቀኝ ሆኖ የመውጣት አደጋ ስላለው በብልሀት ፣ በማስተዋል ሊቀነቀን ይገባል ። በዛድባሬ ይመራ የነበረው "የታላቋ ሶማሊያ" አክራሪ ብሔርተኝነት ለዚህ ጥሩ አብነት ነው፡፡ የናዚው አዶልፍ ሒትለር የአርዓያም ዘር ልፋፌ ነቢብ በዓለማችን ላይ ያስከተለው እልቂትና ቀውስም አይዘነጋም።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥንታዊ መሆኗን የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። ከ3000 እስከ 8000 ዓመት የሚደርስ ታሪክ ባለጸጋ እንደሆነች ይታመናል። ጥንታዊነቷ የዳበረ ሀገረ መንግሥት ባለቤት አድርጓታል። የደለቡ ባህላዊ ወረቶች መናኸሪያም ናት። ባህል፣ ባህላዊ ንብረትስ ምንድን ነው የሚለውን ለመግባቢያ ያህል እንመለከታለን። ባህል ሁሉንም የሚያስማማ የሚያግባባ ወጥ የሆነ ትርጉም ብያኔ ባይኖረውም የአንድ ማኅብረሰብ ወይም ሕዝብ ዕምነት፣ ልማድ ፣ ወግ በኪነ ጥበብ እና በሥነ ጥበብ ተዳውሮ፣ ድርና ማግ ሆኖ ፣ ተሸምኖ፣ ተንሰላስሎ የመገኘት ፣ የመገለጥ ዥጉርጉር ሕብራዊ ደማቅ ቀለም ነው።

በደስታ ፣ በሀዘን ፣ በሥራ ፣ በሃይማኖት፣ በትምህርት ፣ ወዘተ... የሕይወት አንጓዎች ይገለጻል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህልን፡- የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ እምነት ፣ ... ። በማለት ሲተረጉመው። የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በበኩሉ ባህል፡- ልማድ፣ ደንብ ሲል ይፈታዋል፡፡

ባህላዊ ንብረት ( cultural capital ) የሚለው ሀረግ ፔሬ ቦርዴው በተባለ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተነሳ የሥነ ኅብረተሰብ ተመራማሪ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ድርሳናት ያትታሉ። ባህላዊ ንብረት በማኅበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ ዕውቀትን ፣ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው። ባህላዊ ንብረት በግለሰብ፣ በማኅበረሰብ ከፍ ሲልም በሕዝብ በሀገር ይሰላል። የበለፀገ ባህላዊ ንብረት ያካበተ ግለሰብ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ከፍ እንደሚያደርገው ሁሉ ያደገ የለማ ባህላዊ ንብረት ያለው ማኅበረሰብ ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ያለ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ባህል ማለትም የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ፣ ልማድ ፣ እምነት ፣ ወዘተ... በሂደት በዕውቀትና በክህሎት እየበለፀገ ፣ እየዳበረ ሲሄድ ለሀገር ሰላም፣ አንድነት ከፍ ሲልም እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተቃራኒው ባህል በዕውቀት ፣ በክህሎት ካልበለፀገ አይደለም ለሀገር ሰላምና ዕድገት መዋል ይቅርና የማኅበረሰቡን እሴቶች ጠብቆ ማቆየት ካለማስቻሉ ባሻገር የዕለት ተዕለት ችግሮችን እንኳ መፍታት የሚሳነው ይሆናል። ባህላዊ ንብረት እንደ ኢኮኖሚያዊ ንብረት ማለትም ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት ተደርጎ ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ እርቅን፣ መነጋገርን ፣ መቀባበልን ፣ መከባበርን ፣ መተባበርን፣ አንድነትን ፣ ወዘተ . እውን ማድረግ ካልተቻለ እንደባከነ እንደከሰረ ሊቆጠር ይችላል።

ሀገርን ሕዝብን ከግጭት ፣ ከቀውስ፣ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር ፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል ፣ ወዘተ . መታደግ አልቻለማ። እስኪ ለአንድ አፍታ ባህሎቻችንን እምነቶቻችንን ወይም ባህላዊ ንብረቶቻችንን ከዚህ አኳይ እንመዝናቸው። ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ሥራ ላይ ውለዋል ! ? አሁን ከምንገኝበት ሀገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል። ታዲያ እነዚህን ባህላዊ ንብረቶቻችንን እንደ ጦር ዕቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት ፣ መመላለስ ለምን ተሳነን !? መልሱ ቀላል ነው። ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጂ አንኖራቸውም። በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም።

ባልንጀራህን ፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚሉ አብርሃማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን ፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን !? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመንን ኢሬቻን በየዓመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን !? መልሱን ለማግኘት ሚስጥሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም። መልሱ ቀላል ነው። እሱም ባህላዊ ንብረቶቻችንን በሳጥን ቆልፈን እንደ ክት ልብስ በየዓመቱ በዓል ለማክበር ስለምናወጣቸው ነው። አናከብራቸዋለንን እንጂ አልከበርንባቸውም። ሥራ ላይ ስላላወልናቸው (ኢንቨስት) ስላላደረግናቸው ነው። ሀገራዊ ሰላምና አንድነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከሳጥን አውጥቶ እያንዳንዱን ዜጋ በፍጥነት ማልበስን ይጠይቃል፡፡

እንደ ገና ስጦታ

ባህላዊ ወረታችን ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል። አዎ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ፣ የሚዋጅ መሆን አለበት። ዘረኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ቂም በቀልን ፣ ደባን ፣ መከፋፈልን ፣ ወዘተ . መቤዠ ፣ መዋጀት አለበት። ባህላዊ ንብረታችንን ይበልጥ በማጎልበት ፣ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ እድላችን ፣ ለነገ ተስፋችን ፣ ለእርቅ ፣ ለሰላም ፣ ለአንድነት ፣ ለሁለንተናዊ ብልፅግና ፣ ወዘተረፈ ልናውለው ይገባል።

ስኬቶቻችንን የምናወድስበት ፣ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አብክረን ማሰብ ያስፈልጋል። የፍቅር ፣ የእርቅ ፣ የሰላም ፣ የአብሮነት ፣ የማካፈል ፣ የመተባበር ፣ የመተጋገዝ ፣ የመረዳዳት ፣ የምስጋና፣ ወዘተረፈ . ባህሎች፣ ልማዶች ፣ ዕምነቶች ፣ ሃይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ንብረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት ሀገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን ፣ ፍቅር ከጎደለን፣ እርቅ ከገፋን ፣ ሰላም ከራቀን ፣ አብሮነትን በቀዬአዊነት ከተካን ፣ ማካፈልን በስስት ከቀየርን፣ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን ፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን ፣ ወዘተረፈ . ምኑን ሙሉኡ ሆነው !?።

ባለፉት አራት ዓመታት ያለፍንባቸው ሀገራዊ ውጣ ውረዶች ፣ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው !? በመሀላችን እየጎነቆለ ያለ ጥላቻ ፣ ቂም በቀል ፣ ልዩነት ፣ ጎሰኝነት ፣ ወዘተረፈ በአብነት ስንመለከት የደለበ ባህላዊ ወረቶች ባለቤት ካለው ሕዝብና ታሪክ የሚጠበቅ አይደለም። ስለዚህ ብርሀነ ልደቱን ከብርሀነ ልደቱ ባሻገር ሌሎች ባህላዊ ወረቶቻችንም በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ልንኖራቸው ልንገልጣቸው ይገባል ።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «የእኛ ሙያ ሰው ከአደጋ ሲሸሽ እኛን ወደ አደጋው ውስጥ የሚያስገባ ነው»

- አቶ ሙሉጌታ ውዱ

በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ባህር ጠለቅ ዋናተኛ

እፀገነት አክሊሉ

የአዲስ አበባ ከተማ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የከተማዋን ነዋሪ ከሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ተጋላጭነትና ስጋት ለመከላከል ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ፈጥኖ በመድረስ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ የሚሰራ ተቋም ነው።

በሌላ በኩልም ኮሚሽኑ በከተማዋ የአደጋ ስጋት ናቸው የሚላቸውን አካባቢዎች በጥናት በመለየት ነዋሪው ራሱን ከአደጋ እንዲጠብቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችንም በማከናወን በኩል ላቅ ያለ ሚናም ያለው ሲሆን፤ በተለይም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች በውሃ የሚወሰዱ ሰዎችን የማዳን ሥራው እንደ ሀገር ከባድ ከመሆኑም በላይ የባለሙያዎቹ ቁጥር በጣት የሚቆጠር ስለመሆኑ ይነገራል።

እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ባለሙያዎችም የወንዞቻችንን ብክለት ችለው ሰው የማዳን ሥራቸውን በአግባቡ የሚሰሩ ቢሆንም፤ እነሱ በተለያየ ምክንያት ሥራውን ቢያቆሙ ግን ተተኪ እንደማይኖራቸው ደግሞ ይነገራል። ምክንያቱም ዘርፉ እውቀት ያለው ስልጠና እንዲሁም የበቁ የሥራ መሳሪያዎችን ስለሚፈልግ ነው። ዛሬ ላይ አራት ያህል የዘርፉ ባለሙያዎች ቢኖሩም ነገ እነዚህ ሰዎች በቦታው ላይ ባይኖሩ ተተኪ የማግኘቱ ነገር ችግር ውስጥ ነው።

ዛሬ የሕይወት ገጽታ አምድ እንግዳችን ያደረግናቸው ባለሙያ ሥራቸው ሕይወትን ከማዳን በተለይም የራስን ሕይወት አደጋ ላይ ጥሎ ለሌሎች በመኖር ውስጥ ያሉ ከጥቂቶቹ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆኑትን አቶ ሙሉጌታ ውዱ ናቸው። አቶ ሙሉጌታ ውዱ በእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በማዕከል ፈልጎ ማዳን ድንገተኛ አደጋዎች ቡድን መሪና ባህር ጠለቅ ዋናተኛ ናቸው።

ተወልደው ያደጉት በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ራያ ቆቦ ወረዳ ካላኮርማ በምትባል አካባቢ ነው። እንደ አካባቢው ልጆች ከብት ጠብቀዋል፤ ተጫውተዋል፤ ቤተሰቦቻቸውንም አገልግለዋል። ከዛም እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢው ወዳለው ሮቢት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሄድ የመጀመሪያውን የትምህርት እርከን ማለትም ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ያለውን አጠናቀዋል። አቶ ሙሉጌታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለማጠናቀቃቸው ይናገራሉ።

«........ውልደቴና እድገቴ ሰሜን ወሎ ራያ ቆቦ ወረዳ ካላኮርማ በምትባል የገጠር ቀበሌ ነው። አካባቢው ላይ እኔ ብቻም ሳልሆን በርካታ ሕፃናት ማደግ ባለብን የገጠር አስተዳደግ አድገን ሥራ ለምደን ቤተሰቦቻችንን አግዘን ኋላም እድሜያችን ለትምህርት ሲደርስ አቅራቢያችን ባለው ሮቢት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከዛም በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታችንን ለማጠናቀቅ ችለናል» ይላሉ።

አቶ ሙሉጌታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አፋር ክልል በመሄድ በውሃ ቴክኖሎጂ ዘርፍ የውሃ ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ውስጥ በመግባት «በወተር ሰፕላይ እና ሳኒቴሽን» የትምህርት መስክ በዲፕሎማ ለመመረቅ በቅተዋል።

ከዚህ የትምህርት ቆይታ በኋላ አቶ ሙሉጌታ ሥራ መቀጠረን አላሰቡም ይልቁንም ሕዝቤን ማገልገል አለብኝ በሚል ወደ ፖሊስነት ሙያ ገቡ። «....ፖሊስነት ለሀገርና ለሕዝብ መወገን ነውና እኔም የዲፕሎማ ትምህርቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ በፖሊስነት የሙያ መስክ ተሰማርቼ ሀገሬንና ሕዝቤን አገለግል ዘንድ ከአካባቢዬ ተመልምዬ ወደ ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋም ሄድኩ።» ይላሉ።



ፎቶ- ገባቦ ገብሬ

በማሰልጠኛ ተቋሙም ከመሰሎቻቸው ጋር በመሆን ተገቢውን ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ በፖሊስነት ተቀጥረው ሥራቸውን ጀምረዋል። አቶ ሙሉጌታ ከእግረኛ ፖሊስነት ጀምሮ በወንጀል መከላከል፣ በአድማ ብተና ፣ በቡድን መሪነትና በሌሎችም ኃላፊነቶች ለአምስት ዓመት ከስድስት ወራት አካባቢ ካገለገሉ በኋላ በራሳቸው ፍቃድ ሠራዊቱን ተሰናብተው ስለመውጣታቸው ያብራራሉ።

«አንዳንድ ሥራዎች ለእንጀራ ብለው ብቻ አይሰሩም ይባላል አዎ አንዳንድ ሥራዎች እንጀራ ከማብላት ባለፈ የሌሎችን ሕይወት መታደግ ብሎም ሰብዓዊነት ጭምር ይሆኑና ሰዎች ይሳቡባበቸዋል። » የሚሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ቀድሞም ቢሆን ወደ ፖሊስ ሠራዊትነት የገቡት «ሀገሬንና ሕዝቤን በምችለው አቅም ማገልገል አለብኝ» ብለው ነበርና ሠራዊቱን በፍቃዳቸው ከተሰናበቱ በኋላ ወደሌላ የማኅበረሰብ አገልግሎት ለገንዘብ ተብሎ ሳይሆን ለመንፈስ እርካታ ጭምር ወደሚሰራበት ተቋም ለመቀላቀል ወሰኑ።

አቶ ሙሉጌታ ወስነውም አልቀሩ በእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ውስጥ በእሳት ማጥፋት የሥራ ዘርፍ ለመቀላቀል ቻሉ። «...እኔ የመረጥኩት ሥራ ምናልባትም ብዙ ሰዎች ተቸግረው ካልሆነ አልያም እንደእኔ የመንፈሳቸው ጥሪ አስቸግሯቸው ካልሆነ በቀር የማይመርጡት የሙያ ዘርፍ ነው» የሚሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ሥራቸው ሰዎች ከአደጋ ሲሸሹ እነርሱ ደግሞ ወደ አደጋው ሰውንና ንብረትን ለማትረፍ ዘለው የሚገቡበት መሆኑን በመጠቆም የሥራውን አስከፊነት ያስረዳሉ።

« ...እሳት ጠዋት የታየን ንብረትና ሰው ለማታ እንዳልነበር የሚያደርግ በጣም ዘግናኝ አደጋ ነው። እንደ ከተማም ብዙ አስከፊ የእሳት አደጋዎችን እናያለን፤ በተቻለ መጠን አደጋው ስር ሰዶ የተባባሰ እንዳይሆን እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ ጥሪው ከደረሰን ሰከንድ ጀምሮ አስፈላጊውን ሁሉ እናደርጋለን። በዚህም እስከ አሁን ብዙ ሰዎችንና ንብረትን ከውድመትና ከሞት ለማትረፍ ችለናል» በማለት ሁኔታውን ይገልፃሉ።

አቶ ሙሉጌታ በፖሊስነት የጀመሩት የሰብዓዊነት ሥራ በኮሚሽኑም ደግመውት እየሰሩ ቢሆንም አሁንም ግን የሌሎች ሙያዎች ባለቤት በመሆን ይበልጥ ወገናቸውን የማገልገል ፍላጎታቸው ጨመረ።

«......የተለያዩ ሙያዎች ባለቤት መሆን እፈልግ ነበር ያንንም ለማሳካት ኮሚሽኑ ጠቅሞኛል፤ አሁን ላይ ኮሚሽን ኦፕሬተርነት ጀምሮ በኮሚሽኑ የሚሰሩ የአደጋ መከላከል ሥራዎችን አብዛኞቹን እሰራቸዋለሁ።» ይላሉ።

‹‹የማሽን ኦፕሬተር ለመሆን የፈለኩት እኔ እሳት ማጥፋትን እሰራለሁ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሥራዎች አስቸኳይ ይሆኑና ባለሙያው ተዘጋጅቶ ማሽኑን ኦፕሬት የሚያደርጉ ሰዎች ግን ላይኖሩ ይችላሉ። በዚህ በቀላሉ መከላከል ስንችል ብዙ ንብረት አንዳንዴም ሕይወት የሚጠፋበት አደጋ ስለሚኖር እሱን ከመከላከል አንጻር ለምን ማሽኑንም ኦፕሬት አላደርገውም?›› በማለት ሥልጠናውን ወስደው ባለሙያ ለመሆን ስለመቻላቸው ያብራራሉ።

አቶ ሙሉጌታ ይህንን ሥራም እየሰሩ ‹‹በቀለም ትምህርቱ መስክም አንድ ርምጃ መራመድ አለብኝ›› ብለው በማሰብ በያርድስቲክ ኢንተርናሽናል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ « በዲዛስተር ሪስክ ማኔጅመንት» የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ስለማግኘታቸውም ያብራራሉ።

«......የሰብዓዊ አገልግሎት በጣም ከሚያስደስቱኝ ተግባራቶች መካከል ግንባር ቀደሙ ነው ብል ማጋነን አይሆንም። ፖሊስ ሆኜም ድንገተኛ ነገሮች (አደጋዎች) በሚከሰትበት ጊዜ በማውቀውና በገባኝ ልክ ለሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ርዳታ እንዲያገኙ የተቻለኝን ድጋፍ አደርግ ነበር። ነገር ግን ወደ እዚህ ተቋም መምጣቴ በሙያው በቂ እውቀትን ይዞ አገልግሎት መስጠት ስለሆነ ከፍ ያለ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የህሊና እርካታ እያገኘሁበት ነው።» ይላሉ።

አቶ ሙሉጌታ ኮሚሽኑ ከሚሰጣቸው የነፍስ ማዳን ሥራዎች ውስጥ አብዛኞቹ ላይ ተሳታፊ ናቸው። ይህ የሆነው ሙያውን አውቀውትና ወደውት ስለሚሠሩት ነው። በሙያና በትምህርት ራሳቸውን ማብቃት ከመቻላቸውም በላይ እንደእርሳቸው እምነት አንድ ሙያተኛ በሄደበት ሁሉ ችግሩን ለመፍታት ሙሉ የመፍትሔ አካል እንጂ ቆይ ለእዚህኛው ችግር እከሌ ይምጣ ብሎ የሚጠቁም (የሚጠራ ) ሊሆን አይገባውም የሚል እምነት አላቸው።

‹‹ከሕክምና ሙያ በስተቀር እኔ ያልተሳተፍኩበት ወይንም ደግሞ ማደረግ የማልችለው ሙያ የለም››

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «የእኛ ሙያ ሰው ከአደጋ ሲሸሽ እኛን...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

የሚሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ‹‹በዚህም ዘርፈ ብዙ ሙያዎች ባለቤት ነኝ ብል ማጋነን አይሆንም›› በማለት ስለራሳቸው ይገልጻሉ።

«......የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ሠራተኛ ለመሆን ከምንም በላይ ቁርጠኝነት ይጠይቃል፤ ምክንያቱ ደግሞ የምናገኛቸው ሰዎች ጉዳት ላይ ያሉ ሀዘንተኞች ከመሆናቸውም በላይ ለእኛ ለባለሙያዎቹም በቦታው ላይ ያለው እያንዳንዱ ነገሮች አደጋ ያላቸውና ሕይወትን አደጋ ላይ ከመጣል ጋር የሚያወራርዱ ይሆናሉ፤ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ሥራን ከግብ ማድረስ መቻል ትልቅ የአእምሮ እርካታን የሚያስገኝ ነው። አሳዛኝ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች የሥራው መገለጫዎች ቢሆኑም ነገር ግን ችግሮቹን ተቋቁሜ ሥራዬን በአግባቡ እየሠራሁ ነው » በማለት ያስረዳሉ።

በፍላጎታቸው ወደ ሥራው ከመጡ በኋላ መጀመሪያ የገጠማቸው ስልጠና ነበር። አቶ ሙሉጌታ ስልጠና ሲባል ከቤታቸው እየመጡ የሚሰለጥኑ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን ለሶስት ወር በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ቤተሰብ እየተጠየቀ የሚሰለጠንበት መሆኑን ሲያውቁ ትንሽ ድንጋጤ ቢጤ ቢሰማቸውም ወታደር ቤት ከሰለጠኑት ጋር ሲነጻጸር የማይደራረስ በመሆኑ ራሳቸውን አረጋግተው የሚወዱትን ሙያ ባለቤት ለመሆን ጥረታቸውን ቀጠሉ።

«.......እሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ስገባ በቀጥታ ሥራው ላይ የሚሰማራ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን አስቀድሞ ከቤተሰብ ተለይተን ለሶስት ወር ያህል መሠረታዊ የሆኑ በጣም ጠቃሚ ሥልጠናዎችን ወስደናል። እኛም የተለያዩ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን እየሠራን ራሳችንን ብቁ እያደረግን ሄድን።» ይላሉ።

ሥልጠናው ላይ የንድፈ ሃሳብ እውቀትን ከጨበጡ በኋላ የተግባር ልምምድ ማድረጋቸውን የሚናገሩት አቶ ሙሉጌታ፤ ጥሩ የሚባል ግንባታ ብሎም ሥራውን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሥራት የሚያስችል ብቃትን አግኝተው ስለመውጣታቸው ይገልፃሉ።

### የሥራ ላይ ቆይታ

አቶ ሙሉጌታ አስፈላጊውን ሥልጠና ካጠናቀቁ በኋላ፤ በቀጥታ የገቡት ወደ ሥራ ነበር። በዚህን የመጀመሪያ የሥራ ውሏቸው የማይረሳ አጋጣሚን አስተናገዱ። "........ሥልጠናውን እንዳጠናቀቅሁ ሥራ የተመደብኩት ቦሌ አካባቢ ነበር፤ ሠፈሩ ስድስተኛ ጣቢያ ይባላል፤ የእኛን ሥራ በጣም የሚገርም የሚያደርገው ከሰዓታት በፊት ሙሉ የነበረ ነገር ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ አደጋ ደርሶበት ይወድማል። እኛ በቶሎ ከደረስን ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ ሊወድም የነበረ ንብረት ይተርፋል፤ ከዚህ አንጻር ሥራውን ገና እንደገባሁ ስመዝነው እውነትም ኅብረተሰቡን ከችግር የማላቀቅ ሥራ በመሆኑ ከልቤ ተደስቼና ከፍተኛ የሆነ የሥራ ተነሳሽነት ኖሮኝ ጀመርኩት» በማለት ይናገራሉ።

አንዳንድ ጊዜ ይላሉ አቶ ሙሉጌታ፤ የሰው ሕይወትም ሆነ ንብረት ማዳን እየተቻለ በኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማነስ፣አድራሻን በአግባቡ ባለመያዝ፣ በቶሎ ወደ ማዕከል ጥሪ ባለማድረግ ከሁሉም በላይ ደግሞ ቤቶች በተቀጣጣይ ነገሮች መገንባታቸው ችግሮች እንደሚያባብሱ እና እነርሱም ብዙም መፍትሔ መስጠት ሳይችሉ ሲቀር በጣም እንደሚያሳዝናቸው ነው የሚያብራሩት።

በእሳት ማጥፋት ሥራው ላይ ከማይረሱት ገጠመኝ መካከል አቶ ሙሉጌታ « ... ቦታው ቦሌ አካባቢ ነው። የቤቶቹ አሠራርም የተጠጋጋና 16 ያህል አባወራዎች የሚኖሩባቸው ቤቶች ናቸው። ቤቶቹ አካባቢ እሳት ተነሳባቸው። የነገሩ ክፉነት ደግሞ አብዛኞቹ ቤቶች በእንጨት የተሰሩና በላያቸው ላይ ላስቲክ የለበሱ ደሳሳ የሚባሉ ጎጆዎች በመሆናቸው፤ ለእሳት አደጋው መባባስ ምክንያት የሚሆኑ ነዳጅና ዘይት ደግሞ በአብዛኞቹ ቤቶች ውስጥ ነበሩ። ከሁሉም አስከፊው ደግሞ ለእሳት አደጋ ጥሪው የደረሰው በጣም ዘግይቶ ነው። ቦታው ለንፋስ የተጋለጠ በመሆኑ ቃጠሎው ተስፋፍቶ ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ ቤቶቹ ሙሉ በሙሉ መውደማቸው በጣም አሳዛኝ ነበር » ይላሉ።

ሥራው በተራም ቢሆን ሳምንቱን ሙሉ የሚሰራ፤ በዓልና የእረፍት ቀናቶችን የማይመርጥ፤ የቤተሰብ እንዲሁም የማኅበራዊ ሕይወት ጊዜ የሚባለውን የሚያሳጣ ቢሆንም፤ አቶ ሙሉጌታ ግን ለሙያው ተገዢ ሆነው በቁርጠኝነትና ከልብ በመነጨ የአገልጋይነት ስሜት ስለሚሠሩ ምንም ቅሬታ እንደሌላቸው ያብራራሉ።

«......የእረፍት ቀኔ ነው፤ ወይም በዓል ነው፤ ብዬ ከሥራ ወደኋላ ብል የሰው ሕይወትና ንብረት ይወድማል። እኔ ግን ያ ነገር ይቅርብኝ ብዬ ራሴን መስዋዕት ባደርግ ለብዙዎች መትረፍ ምክንያት እሆናለሁ። የእኔ መኖር ለሌሎች ዋጋ የሚያስገኝ ከሆነ ኑሮዬን ከሥራዬ በታች አድርጌ እየሠራሁ ስቆይ ከፍ ያለ የህሊና እርካታ ይሰማኛል» ይላሉ።

### ወደ ባህር ጠለቅ ዋናተኛ

አቶ ሙሉጌታ በእሳት ማጥፋቱ ላይ ከሰሩ በኋላ አብዛኛው ሠራተኛ ወደማይፈልገው ግን ደግሞ እጅግ በጣም አስፈላጊ ወደሆነው የባህር ጠለቅ ዋና ሙያ ለመሄድ ራሳቸውን ማሳመን ፈለጉ። ወትሮም ቢሆን ከፍ ያለ ሰብዓዊነት የነበራቸው አቶ ሙሉጌታ ከእሳት ማጥፋቱ በበለጠ፤ በዚህ ሙያ ቢሰማሩ የብዙዎችን ሕይወት አትርፈው እንዲሁም የተጨነቁ ቤተሰቦችን አግዛለሁ ብለው በማሰብ ወደ ሥራ ገቡ።

«.......አብዛኛው ሠራተኛ ይህንን የሙያ ዘርፍ አይፈልገውም። ምክንያቱም የእኛ ሀገር ውሃዎች አስተማማኝነታቸው ዝቅተኛ ነው። የተበከሉ ናቸው። የመጸዳጃ ቤትና የፋብሪካ ፍሳሾች ጋር የተገናኙ ናቸው። ሰው የሚሳበው ደግሞ የተሻለ ክፍያና የሥራ ላይ ደኅንነትና የሥራ ቦታን መርጦ ነው። እኔ ግን ውስጤን የሚያረካኝ ሰው በተቸገረበት ወቅት ያንን አገልግሎት ሰጥቼ እረፍት መስጠት አለብኝ የሚለው በመሆኑ የተቸገረን ለመርዳት የበኩሌን መወጣት አለብኝ በማለት እንዲሁም ለአደጋ ሥራ ሄጄ ይህንን አልችልም ላለማለት ሁለቱንም አገልግሎቶች ለመስጠት ነው።» በማለት ያብራራሉ።

ጎርፍ ሲከሰት ሐይቅ ውስጥ ሰው ሲገባ አደጋ ደረሰ ተብሎ በረው ከደረሱ በኋላ ሙያተኛ ይምጣ ብሎ ጊዜ መውሰዱ በጣም እንደሚያሳቅቃቸው የሚናገሩት አቶ ሙሉጌታ፤ ይህንን ባለመፈለግም ራሳቸውን ሙሉ ለማድረግ የባህር ጠለቅ ሙያተኛን ስልጠና ወስደው የሥራ ዘርፉን ተቀላቀሉ።

በሀገር ደረጃ በዚህ ሙያ ላይ ያሉ ሰዎች ውስን ናቸው። አቶ ሙሉጌታ ከላይ በጠቀሷቸው ምክንያቶችና ሙያው የሚያስፈልገውን ትኩረት ባለማግኘቱ አሁንም ቢሆን የባህር ጠለቅ ዋናተኛ ባለሙያ የለም ቢባል ይቀላል። አቶ ሙሉጌታ «........ በዚህ ሙያ ላይ ያለፉ አንድ የእኛ የሥራ ባልደረባና መከላከያ ውስጥ ደግሞ አንድ ሰው ነበሩ። እነሱም በጋራ በመሆን እኔና ሰባት ጓደኞቼን አሰልጥነውናል። የመጀመሪያው ራስን የማብቃት ብሎም የመንሳፈፍ ስልጠና የወሰድነው በጊዮን ሆቴል ሲሆን በመቀጠል ባቡጋያ ሐይቅ በመሄድ ሰልጥነናል። ዛሬ ላይ ግን ሥልጠናው በሀገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ቆሟል፤ አይሰጥም።» ይላሉ።

አሁን ላይ በዘርፉ አቶ ሙሉጌታን ጨምሮ አራት ሰዎች ብቻ ያሉ ሲሆን፤ እርሳቸውም የእሳት አደጋ መኪና አሽከርካሪነት ስልጠና ወስደው እሱን ሲሰሩ እርሳቸውን የሚተካ ባህር ጠለቅ ዋናተኛ ጠፋ። መሥሪያ ቤቱም ሁለቱንም ሥራ ጎን ለጎን እንዲሰሩ አደረገ። አሁንም ቡድን መሪ ቢሆኑም ባህር ጠለቅ ባለሙያው ቁጥር በጣም አናሳ ስለሆነ ችግሮች በሚከሰቱና ጥሪ በሚደርስበት ጊዜ ከቢሮ ወጥተው ይሰራሉ።

አቶ ሙሉጌታ ለሙያ ከፍ ያለ ፍቅር ያላቸው ከመሆኑም በላይ በሀገር ደረጃ ባህር ጠለቅ ዋናተኞች ቁጥር በዚህን ያህል አናሳ መሆኑ ያሳስባቸዋል። እናም እንደ መፍትሔ እርሳቸውና በሥራ ላይ ያሉ ባልደረቦቻቸው የአሰልጣኝነት ሥልጠና ተሰጥቷቸው ባለሙያዎችን የማብቃት ሥራ መሥራት እንደሚፈልጉ ይናገራሉ።

ባህር ጠለቅ ዋናተኝነት ሰዎች በጎርፍ ሲወሰዱ ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም ተፈላጊ ሙያ ነው ካሉ በኋላ፤ ‹‹እኛም እንደ ሀገር በአደጋ ብቻ ሳይሆን ትልልቅ ሀይድሮሊክ ፓወሮች በደለል ሲደፈኑና ሌሎችም ችግሮች ሲኖሩ ገብተን የምናጸዳና ችግሩን የምንፈታ ነን›› በማለት ይናገራሉ።

### የሙያው ተግዳሮት

አንዳንድ ሥራዎች በራሳቸው በአደጋ የተሞሉና ከባድ ናቸው። አቶ ሙሉጌታ የተሰማሩበት የድንገተኛ አደጋ ዘርፍ ደግሞ ከሁሉም የባሰ ከባድ አስቸጋሪ ራስን አደጋ ላይ ጥሎ ሌሎችን ለማትረፍ የሚደረግ ግብግብ ነውና አስቸጋሪነቱ በቃላት የሚገለጽ አይደለም።

«.......ሰው ሰራሽ የወንዞች ብክለት የሙያ ከፍተኛው አስቸጋሪ ጎን ነው። ይህ ሲባል የተጠራቀሙ ውሃዎች ላይ የተለያዩ ኬሚካሎችን ይደፋሉ። የመጸዳጃ ቤት ፍሳሾች ከወንዞች ጋር ይገናኛሉ። እንደዚህ ባሉ ወንዞች ላይ ደግሞ አደጋ ደርሶ ለማውጣት በምንሄድበት ጊዜ የተበከለ ውሃ ውስጥ ለመግባት እንገደዳለን።» በማለት ይናገራሉ።

> ውሃዎች ላይ የተለያዩ ኬሚካሎችን ይደፋሉ። የመጸዳጃ ቤት ፍሳሾች ከወንዞች ጋር ይገናኛሉ። እንደዚህ ባሉ ወንዞች ላይ ደግሞ አደጋ ደርሶ ለማውጣት በምንሄድበት ጊዜ የተበከለ ውሃ ውስጥ ለመግባት እንገደዳለን

ይህም ቢሆን ግን አቶ ሙሉጌታ እስከ አሁን ድረስ በተበከሉ ወንዞቻችን ምክንያት የደረሰባቸው የጤና ችግር ባይኖርም በቀጣይ ግን ለሙያው ትኩረት በመስጠት ግብዓት በማሟላት በኩል ሁሉም ድርሻውን ቢወጣ የሚል ሃሳብ አላቸው።

### ገጠመኞች

«.....ብዙ ጊዜ ያልጠበቅነው ነገር ይገጥመናል፤ ልክ ሰልጥኜ መጥቼ የመጀመሪያ ሥራዬን ለመሥራት ወጣሁ፤ አሰልጣኞችን አብሮን ነበርና ልግባ ስለው ግባ አለኝ፤ እሺ ብዬ ገባሁና ሁለት ጊዜ እንደዋኘሁ የጠለቀውን ሕፃን ልጅ አገኘሁት። ሰው መሆኑን አረጋግጬ እዛው ትቼው ስወጣ አሰልጣኜ በመደናገጥ ምን ሆንክ ሲለኝ አገኘሁት አልኩት የት አለ ሲለኝ ውስጥ ነው ላውጣው አልኩት አሰልጣኙም እና ምን ልታደረግ ገባህ ብሎ በመሳቅ ልጁን አወጣሁት። ይህም የመጀመሪያ ሥራዬ ነበር።» በማለት ከማይረሱት አንዱን አጋጣሚዎቻቸው ይናገራሉ።

ሌላው ደግሞ ይላሉ አቶ ሙሉጌታ «......አዲስ አበባ ውስጥ ጎጃም በረንዳ አካባቢ ነው። አንዲት ሴት ቤቷ ግማሽ አካሉ ከወንዙ ወዲህ ግማሹ ከወንዙ ወዲያ ሆኖ በእንጨት ረብራብ ላይ የቆመ ነው፤ የእኛ ተቋምም በጥናት በተደገፈ ሁኔታ ለአደጋ ተጋላጭ ነሽና መነሳት አለብሽ ብሎ በተደጋጋሚ አሳስቧታል። ነገር ግን መሥሪያ ቤቱ ተለዋጭ ቤት የሚሰጣት መስሏት እዛው እየኖረች አንድ ቀን ቤቱ ውስጥ ከልጆቿ ጋር እንዳለች ኃይለኛ ዝናብ ዘንቦ ቤቱን ይዞት ሄደ፤ ለእኛም ጥሪ ደረሰን። በሥፍራው ስንገኝ ቤቱ የለም ፍለጋ ጀመርን። ወንዙ መዳረሻ ድረስ ሄደን ፈለግን፤ ነገር ግን ምንም ማግኘት አልቻልንም ነበር። በማግሥቱ የአንዱን ልጇን አስከሬን አገኘን ነገር ግን ሕፃኗንና እናቷ ሳይገኙ ቀሩ ይህ በጣም ልቤን የሰበረው የሥራ አጋጣሚዬ ነው።» በማለት ያስረዳሉ።

### የቤተሰብ ሁኔታ

አቶ ሙሉጌታ ራሳቸውን ለሰብዓዊነት የሰጡ ቢሆንም ቤተሰብ መመሥረት ላይም ጥሩ ሥራ ሰርተዋል። በዚህም ትዳር መስርተው የሁለት ልጆች አባት ሆነዋል። ባለቤታቸው ሥራቸውን የሚረዱ ከመሆናቸውም በላይ ልጆቻቸውም ሥራውን አውቀው እንደሚደግፏቸው ይናገራሉ።

### መልዕክት

በሙያው ላይ በቂ ግንዛቤና ችሎታ ያስፈልጋል። ሙያው በጣም ተፈላጊ ቢሆንም የተሰጠው ትኩረት ያን ያህል ባለመሆኑ በቂ ባለሙያዎችን ማፍራት ተችሏል ለማለት ይከብዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ሰው ዋና ቢለምድ ቢችል ቢያንስ አነስ ካሉ አደጋዎች እንኳን ራሱን ማውጣት ይችላልና እንደ ቀላል ባይታይ ደስ እንደሚላቸው ተናግረዋል።


በሌላ በኩልም ለሙያው ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ማሰልጠን የሚያስችሉ ቦታዎች ቢኖሩ፤ አሰልጣኝ ባለሙያዎችም ቁጥራቸው ቢበራከት፤ ግብዓቶች በተገቢው ሁኔታ ቢሟሉ ሥራው ከዚህ በላይ ያድጋል በማለት ሃሳባቸውን አጠቃለዋል።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# ታላላቅ በዓላትን - ለላቀ ቱሪዝም ፍሰት

**ዳግም ከበደ**



በቅዱስ ላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በሚከበረው የገና በዓል ላይ ከክርስትና እምነት ተከታዮች በተጨማሪ በርካታ ቱሪስቶችም ይታደሙበታል

በኢትዮጵያ ታኅሣሥና ጥር በድምቀት የሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት እንዲሁም ባህላዊ ትዕይንቶች ይዘወተርባቸዋል። በተለይም በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በልዩ ድምቀት የሚከበሩት የገና እና የጥምቀት በዓላት ብዙ ሚሊዮኖች በአደባባይ ተገኝተው የሚሳተፉባቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ለቱሪዝም መስህብነት የሚጠቀሱ ፌስቲቫሎች ናቸው።

በዚህ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ቱሪስቶች ከሌሎቹ ወቅቶች በተለየ ቁጥራቸው እንደሚጨምር መረጃዎች ያመለክታሉ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በገና እና ጥምቀት የሚከናወኑት ሃይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት ያላቸው ክዋኔዎች እንደሆኑ ይጠቀሳል።

በዩኒስኮ የማይዳሰስ ቅርስ የተመዘገበው የጥምቀት በዓል፤ በታሪካዊቷና በውቅር አብያተ- ክርስቲያናቶቿ በምትታወቀው በላሊበላ ከተማ በዛሬው እለት በልዩ ድምቀት የሚከበረው የገና (የክርስቶስ ልደት) በዓል ሥነ-ሥርዓት ለቱሪስት ቁጥሩ መጨመር ምክንያት እንደሆኑም ይታመናል።

እነዚህ በዓላት ዘንድሮም በልዩ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት ተገኝቶ እንደሚጎበኛቸው ይጠበቃል። ለዚህም በተለይም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እና የቱሪዝም ሚኒስቴር እንግዶችን ተቀብለው ለማስተናገድ ዝግጅታቸውን ስለመጨረሳቸው ከተቋማቱ በተለያየ ጊዜ የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ዘንድሮ በድምቀት የሚከበሩትን እነዚህን በዓላት አስመልክተው የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ለዝግጅት ክፍሉ እንደገለጹት፤ ዛሬ የሚከበረውን የገና በዓል እና በጥር ወር የሚከበረውን የጥምቀት በዓል በደማቅ ሥነ-ሥርዓት ለማክበር በሚኒስቴሩ በኩል በቂ ዝግጅት ተደርጓል። ሁለቱ በዓላት ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በስፋት ይከበራሉ። በዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጎብኚዎች ወደተለያዩ ቦታዎች በመሄድ መጎብኘት እንዲችሉ የቱሪስት መዳረሻዎቹ ክፍት ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረገ ይገኛል።

ለአብነትም ከገና በዓል ጋር በተያያዘ ወደ ላሊበላ ከተማ በርካታ ጎብኚዎች እንደሚሄዱ ጠቅሰው፣ የበዓሉን አከባበር አስመልክቶ ከከተማዋ ከንቲባና ከቤተክርስቲያናቱ አስተዳዳሪ ጋር ውይይት መደረጉን ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል። ወደ አካባቢው የሚሄዱ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ በቂ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

የታኅሣሥ እና ጥር ወራት በርካታ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡባቸው ወቅቶች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በዋናነትም የገና እና የጥምቀት በዓልን ተከትሎ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ፍሰት እንደሚጨምርም ነው ያስረዱት።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ ሁለቱ በዓላት በሌላው ዓለም በስፋት የማይከበሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ጎብኚዎች ፍሰት እንደሚጨምር ይጠበቃል። በተጨማሪም አብዛኛው የዓለም ሀገራት በአሁኑ ሰዓት አዲስ ዓመትን ተከትሎ እረፍት ላይ መሆኑ የጎብኚዎችን ቁጥር ይበልጥ ከፍ ሊያደርገው ይችላል።

በዓላቱን ምክንያት አድርገው ለሚመጡ ቱሪስቶችም አማራጭ የጉብኝት ጥቅሎች እንዲኖሩ መሠራቱን ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ስለሺ ጠቁመዋል። ከፀጥታ ጋር ተያይዞ ያለውን ስጋት ለማስቀረት ቱሪስቶች በኦንላይን መረጃ ማግኘት የሚችሉበትን የሞባይል መተግበሪያ በማልማት ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉንም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማህበር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ክብሮም ተስፋይ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ማህበሩ የተመሠረተው በዘርፉ ኤክስፐርት በሆኑና በቂ የሙያ ትምህርትና ሥልጠና በወሰዱ አስጎብኚ ባለሙያዎች ነው። ማህበሩ 250 አባላት ያሉት ሲሆን፣ ከተመሠረተ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል።

‹‹ከመስከረም እስከ መጋቢት ያለው በኢትዮጵያ የቱሪስት እንቅስቃሴ በስፋት የሚታይበት ነው›› የሚሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የገና እና ጥምቀት በዓላት ዋንኛዎቹ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። በየዓመቱ የውጪ ቱሪስቶች እንዲመጡ የሚደረግበት ስልት እንደሚለያይ በማንሳትም በዘንድሮው የታኅሣሥና ጥር ወራት የተለየ እቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን ያመለክታሉ።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጠረውን የሰላም መደፍረስ ተከትሎ የጎብኚዎች መጠን እንዳይቀንስ የሚያደርጉ የተለያዩ ሥራዎች በትኩረት እየተሰሩ ናቸው። በዋናነትም ሰላማዊና ደህንነታቸው በተረጋገጠ አካባቢዎች ላይ ቱሪስቱ እንዲጎበኝ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው።

ይህ ዓይነቱ አሰራር በሌሎች ሀገራትም እንደሚተገበር ጠቅሰው፣ በየትኛውም የዓለም ክፍል ላይ ፍፁም የሆነ ሰላም እንደሌለም ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ ጎብኚዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ በገና እና የጥምቀት ልዩ በዓላት ላይ እንዲታደሙ እንደ አስጎብኚ ማህበሩ አቅጣጫ ይዞ እየሰራ መሆኑን ይናገራሉ።

‹‹ቀደም ባሉት ዓመታት በታኅሣሥ እና ጥር ወራት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ጎብኚ ወደ ሀገሪቱ ይገባ ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት ግን በኮቪድና በአንዳንድ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች መቀነስ ይታያል›› የሚሉት አቶ ክብሮም፤ አሁንም ግን ጥቂት የማይባል ቁጥር ያለው ቱሪስት በዓላቱ ላይ ለመታደምና ለመጎብኘት እንደሚመጣ ይገልፃሉ።

አቶ ክብሮም እንዳሉት፤ ባለፉት ሁለት ወራት የቱሪዝም ማኅበረሰቡ ባደረገው ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራ ምክንያት ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ ጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምር ምክንያት ይሆናል። ይህ ወቅት ከዚህ ቀደም በዚህ ወቅት ከሚመጣው ቱሪስት አንፃር ምንም እንኳን ዝቅ ያለ ቁጥር የሚመዘገብበት ቢሆንም፣ ካጋጠመው ችግር አንፃር ግን ተስፋ ሰጪ የጎብኚዎች ቁጥር ሊኖር ይችላል። እነዚህ ጎብኚዎችን የማህበራቸው አባላት የሆኑ አስጎብኚዎች በኢትዮጵያዊ ጨዋነት፣ በጥሩ መስተንግዶና ፍትሃዊ በሆነ ዋጋ ለማስተናገድ ዝግጅት አድርገዋል።

እንደ አቶ ክብሮም ገለፃ፤ በተለይ ከዚህ ቀደም የጎብኚዎች መዳረሻ የሆኑ ሥፍራዎችና ተዘግተው የቆዩ አካባቢዎች እንዲነቃቁ ለማድረግ እየተሠራ ነው። በተለይ ለጎብኚዎች ጥሩ የክፍያ ዋጋ በማቅረብ ፍላጎት እንዲያድርባቸውና በብዛት እንዲመጡ ለማድረግ፣ በመስህብ ሥፍራዎቹ የሚገኙ ሆቴሎች እንዲሁም አገልግሎት ሰጪዎች እንዲነቃቁና በተሻለ ቅልጥፍና እንግዶችን እንዲቀበሉ ውይይት ተደርጓል።

ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በኢትዮጵያ የሚከበሩትን የገና እና የጥምቀት በዓላት ለማክበር የሚመጡ ቱሪስቶች የቆይታ ጊዜያቸውን ወስነው ላይመጡ ይችላሉ። ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ልዩ ልዩ አማራጮችን በማሳየት ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ ማድረግ ይቻላል። ይህንን በተመለከተ ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ከዋናው በዓል በተለየ ጎብኚዎች ቆይታቸውን አራዝመው ሌሎች መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ ለማድረግ እንደሚሰራ ይናገራሉ።

‹‹በዚህ ወቅት በዋናነት ከሚጎበኙት መስህቦች ባሻገር አዳዲስ መዳረሻዎች በቱሪስቱ እንዲታዩ እየሠራን ነው›› ሲሉ ገልጸው፣ አዳዲስ የተሰሩ መዳረሻዎች ምን ዓይነት ይዘት እንዳላቸው ለማየት የማህበሩ አባላት በአካል ተገኝተው በቅድሚያ መጎብኘታቸውን ያስረዳሉ።

ይህም ለዝግጅት እንደረዳቸውና ቱሪስቶችን ወደ ስፍራው እንዲያቀኑ ለማድረግ እድሉን እንዳመቻቸላቸው ያመለክታሉ። በልዩ ልዩ መዳረሻዎች በመገኘት መዳረሻዎቹን በፎቶና ተንቀሳቃሽ ምስል በመውሰድ፣ ርቀታቸውን የመለየት ዝግጅት እንዳደረጉም አስታውቀዋል።

ቱሪዝም በርካታ ጉዳዮች በአንድ ላይ ተካትተው በጥቅል ለቱሪስቱ የሚቀርብ አገልግሎት መሆኑን አቶ ክብሩ ጠቁመው፤ በዚህ ውስጥ በርካታ ባለድርሻዎች በአንድ ላይ እንደሚሳተፉ ይናገራሉ። ስኬታማ መሆን የሚቻለውም አየር መንገዱ፣ ቱር ኦሬተሮች፣ አስጎብኚው፣ አገልግሎት ሰጪ ሆቴሎች፣ መዳረሻው የሚገኝባቸው ክልሎች፣ ሚኒስቴሩ እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሲሰሩ መሆኑን ይናገራሉ።

በመሆኑም በእነዚህ ትላልቅ በዓል በሚከበርባቸው ጊዜያት በጋራ ለአንድ ዓላማ መሥራት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። በዚህ ረገድ በተለይ የገና እና ጥምቀት በዓላት በስኬት እንዲጠናቀቁም ማህበሩ ከእነዚህ አካላት ጋር ለመሥራት መዘጋጀቱን ነው ያስረዱት።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ከፍተኛ የቱሪስት እንቅስቃሴ በሚደረግባቸው በእነዚህ ወራት በውጭ ሀገሮች ለሚኖሩት የ‹‹ሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን›› ወደ ሀገራቸው እንዲገቡና ከባህላቸው ከታሪካቸው ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ጥሪ ማድረጉን ይገልፃሉ። ይህም ለቱሪዝሙ ተጨማሪ እድል መሆኑን ነው ያመለከቱት። ስለ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም እውቀቱ የሌላቸው ዜጎች ወደ ሀገራቸው ገብተው ከማኅበረሰቡ ጋር እንዲገናኙ የማድረጉ ሃሳብ ጥልቅና አስፈላጊ መሆኑን ያነሳሉ። በተለይ ታላላቅ ክዋኔዎች የሚታዩበት የገና እና ጥምቀት በዓላት እንዲገኙ ጥሪ መደረጉም በራሱ አጋጣሚውን ልዩ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።

‹‹ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ጥሪ የተደረገላቸው የሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ወጣቶች የዲጂታል ዘመኑን ጠንቅቀው የሚረዱ ናቸው›› ያሉት አቶ ክብሮም፤ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ዓለምን ማዳረስ የሚያስችል እውቀት የታጠቁ መሆናቸውንም ይገልጻሉ። ይህ ወጣት ኃይል በዲጂታል አማራጭ የኢትዮጵያን ቱሪዝም ማስተዋወቅ እና የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር የማድረግ አቅም ያለው ኃይል እንደሆነ ይናገራሉ። በተለይ በእነዚህ ልዩ ክብረ-በዓላት ላይ ሲገኙ በዲጂታል አማራጭ የሚያሰራጯቸው መረጃዎች ተፅዕኖ የሚፈጥሩና የኢትዮጵያን መልካም ገፅታ የሚገነቡ እንደሚሆኑም ያስረዳሉ።

አቶ ክብሮም እንደሚሉት፤ በዚህ ወቅት ጥሪ የተደረገላቸው በውጭ ሀገሮቹ የሚኖሩ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያላቸውን እውቀትና ሀብት በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ላይ ማዋል የሚችሉ ናቸው። ከዚህ የተነሳ ማህበሩ መንግሥት ያደረገው ጥሪ እንዲሳካና ወደ ሀገራቸው የሚገቡ ኢትዮጵያውያን የመጡበትን ዓላማ እንዲያሳኩ እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ይሰራል። በተለይ የሀገራቸውን ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስና ተፈጥሮ ጠንቅቀው እንዲያውቁ በየመጡበት ሀገር ቋንቋ ለማስረዳትና ለማስጎብኘት ማህበራቸው ዝግጅቱን አጠናቋል።

አቶ ክብሮም ‹‹በዓሉ ለእምነቱ ተከታዮች ምህረት እና ፀሎት የሚያደርግበት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን፣ የእምነቱ ተከታይ ላልሆኑት ደግሞ የአብሮነት፣ የብዝሀነትና የውበታቸው ምልክት ነው›› ይላሉ። በዓሉን አስመልክቶ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ጎብኚዎች የሃይማኖቱን ተከታዮች ብቻ ሳይሆን የሚጠቅሙት መላ ሀገሪቱን እንደሆነ አንስተው፤ ሁሉም እሴቶቹን በጋራ መጠበቅና የእኔነት ስሜት መፍጠር ይገባዋል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ንጉሥ ላሊበላ እና የገና በዓል

ዋስልኝ አየለ



ከዛሬ 896 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በገና በዓል ዕለት ታኅሣሥ 29 ቀን 1120 ዓ.ም አጼ ላሊበላ ተወለዱ:: የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ እነሆ 850 ዓመታት ሆናቸው:: ንጉሥ ላሊበላ እነሆ በዚህ ዓለም አቀፍ ንብረት በሆነው የላሊበላ ሚሊኒየም ተሻጋሪ ቅርስ ሲታወሱ ይኖራሉ:: በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 900 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን ንጉሥ ላሊበላን እናስታውሳለን:: ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ ክስተቶችን እናስታውስ::

ከ99 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃንና የጋዜጠኝነት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የነበረው ‹‹ብርሃንና ሰላም›› ጋዜጣ ተመሰረተ (ለሕትመት በቃ):: አንጋፋው ‹‹ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት›› መስከረም 3 ቀን 1914 ዓ.ም በንጉሥ ተፈሪ መኮንን (በኋላ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ) መኖሪያ ግቢ ውስጥ ጨው ቤት በሚባለው ባለ ሁለት ክፍል ውስጥ ሥራውን ጀመረ:: ማተሚያ ቤቱም ታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ.ም “ብርሃንና ሰላም” የተባለውን ጋዜጣ ማተም ሲጀምር ስሙም ከዚሁ ጋዜጣ ወረሰና ‹‹ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት›› ተባለ:: ይህም ማተሚያ ቤቱ ጋዜጦችን እንዲያትም (የማተም አገልግሎት እንዲሰጥ) አስቻለው::

‹‹ብርሃንና ሰላም›› ጋዜጣ በ500 ቅጂዎች ያህል በሳምንት አንድ ጊዜ (ሐሙስ ዕለት) ይታተም፤ የስርጭቱም በሁለት ፈረሰኞች አማካኝነት ይካሄድ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳል።

ጋዜጣው ሲመሠረት (ከ1917) ጀምሮ እስከ 1921 ዓ.ም ድረስ የጋዜጣው ዳይሬክተር (ዋና አዘጋጅ ለማለት ነው) የነበሩት አቶ ገብረክርስቶስ ተክለሃይማኖት የተባሉት የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ነበሩ:: በ1921 ዓ.ም አቶ ማኅተመወርቅ እሸቴ የጋዜጣው ዳይሬክተር ሆኑ::

ጊዜው ለኢትዮጵያ የብርሃንና የደስታ (ሰላም) እንዲሆን በመመኘት (በማሰብ) ንጉሥ ተፈሪ መኮንን የጋዜጣውን ስያሜ ‹‹ብርሃንና ሰላም›› ብለው እንደሰየሙት ይነገራል።

ሌላኛው የዚህ ሳምንት ክስተት ከ27 ዓመታት በፊት ታኅሣሥ 23 ቀን 1989 ዓ.ም ጋናዊው ዲፕሎማት ኮፊ አናን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 7ኛው ዋና ፀሐፊ ሆነው ተሾሙ:: በተለይም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋዜማ የኮፊ አናን ስም በተደጋጋሚ ይጠራ ነበር:: ምክንያቱም ያ ወቅት ኮፊ አናን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊነቱን ያጠናቀቁበት ወቅት ነበር::

ከ6 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 23 ቀን 2010 ዓ.ም በዘመናዊ የኢትዮጵያ የሕክምና ታሪክ ጉልህ ስፍራ ያላቸው፣ ስለበሽተኞች የምርመራ ሪፖርት አያያዝ የሚያስረዳ በኪስ የሚያዝ መመሪያ (A Guide to Write Writing Medical Case Reports) አዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውል ያደረጉት፣ ፕሮፌሰር ዶክተር ዕደማርያም ፀጋ አረፉ::

ከ121 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 24 ቀን 1895 ዓ.ም የፊደል ገበታ አባት የሚባሉት እና አርበኛው ቀኛዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ ተወለዱ:: ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ የአማርኛ ፊደል ሆሄያትን በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ለማስተማር በእግራቸው ብዙ የዞሩ እና ያስተማሩና “የፊደል አባት” የሚል ማህበራዊ ማዕረግን ያገኙ ሰው ናቸው:: በጣሊያን ወረራ ወቅትም ከፍተኛ የአርበኝነት ሥራ ሰርተዋል::

ከ6 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የመጀመሪያው አፍሪካዊ ‹‹የንግድ ጄት›› አብራሪ የሆኑት ኢትዮጵያዊው ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ አረፉ::

ካፒቴን ዓለማየሁ ገና ከአስር ዓመታቸው ጀምሮ አውሮፕላን በሰማይ ላይ ሲበር ሲያዩ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ሕልም እንደነበራቸው በተለያዩ ፀሐፊያን የተሰነደው ታሪካቸው ያሳያል:: ህልማቸውን ለማሳካት ጠንካራ ትጋትና ሥነ ምግባር የነበራቸው ካፒቴን ዓለማየሁ፣ በ1955 ዓ.ም የመጀመሪያውን ‹‹የንግድ (Commercial) ጄት›› በማብረር በዘርፉ ፈር ቀዳጅ ኢትዮጵያዊ፤ እንዲሁም አፍሪካዊ ለመሆን በቅተዋል::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ወደ ጄት ዘመን ሲሸጋገር ከፋና ወጊ አብራሪዎች ተጠቃሹ ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ ነበሩ:: የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ‹‹ቦይንግ 720B›› አውሮፕላን በካፒቴንነት ያበረሩት ካፒቴን ዓለማየሁ፣ በዚሁ ተግባራቸው ‹‹የመጀመሪያው›› አፍሪካዊም ናቸው:: በኅዳር 1955 ዓ.ም ቦይንግ ጄት ከሲያትል (አሜሪካ) ከቦይንግ ፋብሪካ አውሮፕላኑን እንዲያመጡ የተደረጉት ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ እና ካፒቴን አዳሙ መድኃኔ ነበሩ::

ካፒቴን ዓለማየሁ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለመቀላቀል የቻሉት በኢትዮጵያ አየር ኃይል በኩል በማለፍ ነው:: በወቅቱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ወደ አቪዬሽን ትምህርት እንዲገቡ ሲደረግ ከዕድሉ ተጠቃሚዎች መካከል አንዱ ካፒቴን ዓለማየሁ ነበሩ:: በ1943 ዓ.ም ምርጥ የሆኑ አብራሪዎች ከአየር ኃይል ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲዛወሩ በተወሰነው መሠረት፣ ካፒቴን ዓለማየሁ ከተመራጮቹ አንዱ መሆን ችለው የኢትዮጵያ አየር መንገድን ተቀላቀሉ::

በሦስት አስርታት ዓመታት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአገልግሎት ዘመናቸውም ከመጀመርያ የበረራ መኰንንነት እስከ ካፒቴንነት (ከየመጀመሪያው የቦይንግ 720B ጄት ካፒቴንነት) እስከ አየር መንገዱ የበረራ ዘርፍ ምክትልና ዋና ኃላፊነት (ከ1948 እስከ 1960 ዓ.ም) ድረስ ሠርተዋል:: ከ1961 እስከ 1972 ዓ.ም. ደግሞ የዓለም አቀፍ በረራዎች ዳይሬክተር፣ የበረራ ኦፕሬሽን ረዳት ጄኔራል ማኔጀር ሆነው አገልግለዋል:: በ1968 ዓ.ም. የመጀመሪያው አፍሪካዊ የቦይንግ 707 ጄት ካፒቴን ሆነው ሲሾሙ፣ በ1972 ዓ.ም የጄት ካፒቴኖች ፈታኝ በመሆን አገልግለዋል::

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አገልግሎታቸውን በ1974 ዓ.ም ፈጽመው ከተሰናበቱ በኋላ፣ በኡጋንዳና በየመን አየር መንገዶች ውስጥ በአሠልጣኝነትና በአማካሪነት ለአምስት ዓመታት ያህል ሰርተው የበረራ ምዕራፋቸውን ቋጭተዋል::

ካፒቴን ዓለማየሁ አበበ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሥራ አስፈፃሚ የነበሩትን ኮሎኔል ስምረት መድኃኔ እንዳስተማሯቸው ታሪካቸው ያስረዳል::

በሦስቱ መንግሥታት ዘመን በከፍተኛ የሀገርና የሙያ ፍቅር ሀገራቸውን ያገለገሉት ካፒቴን ዓለማየሁ፣ ባለትዳርና የአራት ሴቶችና የአራት ወንዶች ልጆች አባት፣ እንዲሁም የአራት የልጅ ልጆች አያት ነበሩ:: ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ በማሰብም በ1997 ዓ.ም ‹‹ሕይወቴ በምድርና በአየር›› የሚል መጽሐፍ አሳትመዋል። የካፒቴን ዓለማየሁ አበበን ታሪክ ትንሽ ዘለግ ያደረግነው የእንዲህ ዓይነት ሰዎች ታሪክ መታወስ ስላለበት ነው::

አሁን ወደ ንጉሥ ላሊበላ እንሂድ:: አጋጣሚ ሆኖ እነሆ ዛሬ የገና በዓል ነው:: በገና በዓል ዕለት ሳምንቱን በታሪክ ገናን እና ንጉሥ ላሊበላን እናስታውሳለን ማለት ነው::

ስመ መንግሥታቸው ገብረመስቀል፤ አንዳንድ ሰነዶች ላይ ደግሞ ገብረክርስቶስ ይባል:: ይህ የ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (1120 ዓ.ም) ታሪክ ነው:: እነሆ ወደ አንድ ሚሊኒየም (1000 ዓመታት) እየተጠጋ ነው:: አጼ ላሊበላ በላስታ ላሊበላ ታኅሣሥ 29 ቀን 1120 ዓ.ም እንደተወለዱ ታሪካቸው ያሳያል:: እነሆ በዚሁ ቅዱስ ቦታ ላይ የገና በዓል በየዓመቱ ታኅሣሥ 29 ቀን በድምቀት ይከበራል:: እንደ ዘንድሮ ባሉ አጋጣሚዎች (ጳጉሜን 6 ስትሆን) ደግሞ ታኅሣሥ 28 ቀን ይከበራል:: ምክንያቱ ሃይማኖታዊ ቀመር ስለሆነ እንለፈውና፤ ታሪካዊ ይዘቱን ምክንያት በማድረግ የዚህ ሳምንት አካል ስለሆነ ስለንጉሥ ላሊበላ ታሪክ ጥቂት እንቃኝ::

የዛግዌ ሥርዎ መንግሥት ንጉሥ ነበሩ:: ለ40 ዓመታት ያህል በንጉሠ ነገሥትነት የቆዩ ሲሆን፣ ታሪካቸው ከ12ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ይዘልቃል::

የንጉሥ ላሊበላ ታሪክ በዋናነት የሚታወቀው የዓለም ሀብት በሆነው የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት ነው:: ከባለቤታቸው እቴጌ መስቀል ክብራ ጋር በመሆን 11 ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን አሰርተዋል:: እነዚህም፤ ቤተ መድኃኒያለም፣ ቤተ ማርያም፣ ጎለጎታ ሚካኤል፣ ኪዳነ ምህረት፣ ሥላሴ፣ ቤተ አማኑኤል፣ ቤተ ሊባኖስ፣ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ መርቆሬስ፣ ቤተ ጊዮርጊስ እና ቤተ መስቀል ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ቤተ ጊዮርጊስ በመስቀል ቅርጽ የተሰራ ነው::

ስለ አጼ (ንጉሥ) ላሊበላ ይህ ታሪክ ይነገራል:: ንጉሡ ላሊበላ የሚለውን ስም ያገኘው፣ ሲወለድ በንቦች ስለተከበበ ነው ይባላል። “ላል” ማለት በአገውኛ ቋንቋ ማር ማለት ሲሆን፤ “ላሊበላ” ማለትም ላል ይበላል (ማር ይበላል) ማለት እንደሆነ ይነገራል። ውቅር ቤተ ክርስቲያናቱን ንጉሡ ጠርቦ የሰራቸው ከመላዕክት እገዛ ጋር እንደሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ይነግራል።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አውሮፓዊው ተጓዥ ላሊበላን ተመልክቶ «ያየሁትን ብናግር ማንም እንደኔ ካላየ በፍጹም አያምነኝም» ሲል ተናግሮ ነበር።

ቅዱስ ላሊበላ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ሕንፃዎችን ለመገንባት አሰበ፤ ከዚያም በጊዜው ከነበሩት አባቶች በተለይ ቀይት ከምትባል ባለአባት የጠየቀውን 40 ጊደር ለመግዛት በሚያስችለው ወርቅ ቦታውን ገዝቶ በከርሰ ምድር ውስጥ ያሉትን ሕንፃዎች ሊያወጣ ተዘጋጁ:: ቅዱስ ላሊበላ የሚገነባባቸውን መሳሪያዎች ለ10 ዓመታት አዘጋጅቶ፤ በ1157 ዓ.ም ነግሶ በ1166 ዓ.ም ሕንፃውን ገንብቶ ጨረሰ:: ቅዱስ ላሊበላ ከ40 ዓመታት የንግስና ዘመን በኋላ በተወለደ በ97 ዓመቱ ሰኔ 12 ቀን 1217 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ (1120 ዓ.ም) እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ (1217 ዓ.ም) ድረስ የዘለቀው የላሊበላ ታሪክ አንድ ክፍለ ዘመን ይሸፍናል ማለት ነው::

ላሊበላ እነሆ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም ቅርስ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ‹‹ገናን በላሊበላ›› በሚል በድምቀት እየተከበረ ይገኛል::

**መልካም የገና በዓል!**

# የዝነኞች ገጽ

## ‹‹ከአንድ የትያትር መግቢያ ዋጋ የአንድ ማኪያቶ ዋጋ ይበልጣል››

- አርቲስት ሄኖክ ብርሃኑ

**ሰሚራ በርሀ**



እጅግ በርካታ ዓመታትን ከትያትር ቤት ሳይርቅ በኪነ-ጥበብ ሙያ ውስጥ ቆይቷል። ትያትር አንዴ ከገቡበት ለመተው የሚቻል ሙያ ስላለመሆኑም ያነሳል። ለዚህም ይመስላል በተለያዩ የቴሌቪዥን ድራማዎች፣ ፊልሞች እና ፕሮግራሞችን በማቅረብ በቴሌቪዥን መስኮት ብንመለከተውም እሱ ግን በተለያዩ ትያትሮች ላይ በመጫወት አሁንም ድረስ በመድረክ ላይ አለ። በዛሬው ዝነኞች ገጻችን ስለ ሥራና ሕይወቱ ስንል እንግዳችን አድርገነዋል።

ውልድት እና እድገቱን ያሳለፈው በደጃች ውቤ ሰፈር ነው። በሰሜን ማዘጋጃም ይኖር ነበር። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በራስ አበበ አረጋይ ትምህርት ቤት የተማረ ሲሆን ተፈሪ መኮንን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደግሞ ኪነ-ጥበብን ‹‹ሀ›› ብሎ የጀመረበት ነው። ለኪነ-ጥበብ መነሻ በሆነው የተፈሪ መኮንን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ቆይታው በአሁን ሰዓት አንጋፋ ከሆኑ ተዋንያን አርቲስት ሽዋፈራው ደሳለኝ እና ሌሎች ባለሙያዎች ጋር ከጅምሩ አብረው ስለመሆናቸው ያነሳል። የዛሬው የዝነኞች ገጽ እንግዳችን ተዋናይ ሄኖክ ብርሃኑ።

ከትያትር ውጪ የሙዚቃ መሳሪያዎች ክራር፣ ኪቦርድ ፣ ድራም የሙዚቃ መሳሪያዎች ይጫወታል። ምክንያቱም የልጅነት ፍላጎቱ ሙዚቀኛ መሆን ነበር። ይህ ፍላጎት ያለ ምክንያት የመጣ አልነበረም። ሄኖክ አሁን ያለበትን ሙያ ከወላጆቹ የወረሰ ይመስላል። አባቱ ብርሃኑ ዮሴፍ ሙዚቀኛ የነበሩ ሲሆን በሀገራችን በቀዳሚነት ከሚጠሩ ባንዶች ውስጥ በሮሀ ባንድ ውስጥ ድራመር፣ በሀገር ፍቅር ትያትር ቤት፣ በኢትዮ ስታር ባንድ፣ በዳዲሞስ ባንድ የሙዚቃ ሥራቸውን ያቀርቡ የነበሩ አንጋፋ የሙዚቃ ሰው ናቸው። እናቱም ወይዘሮ አስቴር ማሞ ተወዛዋዥ እና ተዋንያን ነበሩ። ከመላኩ አሻግሬ ጋር በመሆን "አንድ ጡት" የሚል ትያትር ሰርተዋል። ‹‹ማጣትና ማግኘት›› የሚል ትያትር ላይ ተውነዋል።

ሄኖክ የአባቱን ፈለግ በመከተል የመሰናዶ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ህልሙን ለማሳካት በሀገራችን የሙዚቃ ትምህርት ቤት ታሪክ ውስጥ በቅድሚያ በሚነሳው የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ለመማር ከአንድ ሺህ በላይ ከሆኑ ተማሪዎች በማወዳደር፤ ከዚያም ከተቀሩት 80 ተማሪዎች ውስጥ አልፎ፣ ቀሪ 30ዎቹ ውስጥ ገብቶ ይወደው የነበረውን የሙዚቃ ትምህርት ለመማር ወደ ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ጉዞውን ጀመረ። ሄኖክ ኪነ-ጥበብ ከልጅነቱ የተሳበበት ነውና በያሬድ የሙዚቃ ትምህርቱን ከመቀላቀሉ በፊት ‹‹ፋቡላ የትያትር ቡድን›› በጊዜው አማተር፣ የአሁን አንጋፋ የትያትር ባለሙያዎች ጋር የተለያዩ የትያትር ሥራዎችን ያቀርቡ ነበር። ይህን ቡድን ያቋቋመው ተፈራ ወርቁ ሲሆን ቡድኑ ብዙ የትያትር ባለሙያዎችን ያፈራ ነው። ቡድኑ የተለያዩ ትያትሮችን እየሰራ ለእይታ ያቀርብ ነበር። ‹‹ድርብ ሀዘን›› በዚህ ቡድን የጊዜው አማተር ተዋንያን የአሁን አንጋፋ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የተጫወተው የሙሉ ሰዓት ትያትር ነበር። ከዚያም ሄኖክ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመሆን ‹‹ገድሉ አሰግደው›› የሚባል የትያትር ቡድን አቋቁመው ‹‹የአባቷ ልጅ›› የተሰኘ፣ በጊዜውም ተወዳጅ የነበረ ትያትርን ለእይታ አቅርበዋል።

ሄኖክ በያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ቆይታው ትምህርቱ ጊዜና ልቦናን መስጠት የሚፈልግ ሲሆን እርሱ ደግሞ በትያትሩ ላይ ይበልጥ እየተሳበ በመምጣቱ ከሙዚቃ ትምህርት ቤት ጥሪው ወደ ሆነው ትያትር ሸፈተ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው፣ ለእርሱ ፕሮፌሽናል የሚለው የትያትር መድረክ "ሮሚዮና ጁሊዬት"፣ "ጁሊዬስ ቄሳር" የተሰኙ ትያትሮች ላይ "ካስት" የተደረገበት ገጠመኝ ነበር። ትያትሩ የሚታይበት ቦታ በማዘጋጃ ቤት ነበር። ከዚያም በተለያዩ ጊዜያት ልምድና ፍላጎትን ተሰጥኦን ባጣመረ መልኩ የትያትር ሕይወቱን ቀጠለ። አሁንም ድረስ የተለያዩ ትያትሮችን በተለያዩ ገጸ-ባህሪያትን ወክሎ እየተጫወተ ይገኛል።

ሄኖክ ከሰራባቸው ትያትሮች ‹‹ሩብ ጉዳይ›› በጣም ተወዳጅ የነበረ ትያትር ነበር። "ትናንሽ ፀሐዮች" እንዲሁ በርካቶች የሚወዱት የማይረሳ የሬዲዮ ድራማ ነበር። ‹‹ማበዴ ነው››፣ ‹‹ሸብ ረብ›› (በፋና ቴሌቪዥን) ሰዎች ልብ ላይ የቀሩ ሥራዎቹ ናቸው።

ሄኖክ ብርሃኑ በኪነ-ጥበብ ውስጥ በርካታ ዓመትን አስቆጥሮ ከሚወደው ትያትርም ሳይጠፋ፣ በፊልሙ ዓለምም እንዲሁ የተለያዩ ፊልሞችን እየሰራ፤ አቅሙንም በማጎልበት የተለያዩ የቴሌቪዥን ድራማዎችና ሌሎች ፕሮግራሞችን እየሰራ ይገኛል። በርካታ ገጸ-ባህሪያትን ወክሎ ለረጅም ዓመታት እየተጫወተ ሲቆይ ግን ለመጫወት የሚመርጠው፤ አልያም በፍጹም መሥራት የማይፈልገው፣ ገጸ-ባህሪ ብሎ የሚለየው እንደሌለ ይናገራል። ‹‹እንደ አንድ ባለሙያ የተሰጠንን ገጸ-ባህሪ መምረጥ ባለሙያ አያስብልም ብዬ አምናለሁ። ትያትር የገሀዱ ዓለም ነጸብራቅ በመሆኑ አንድ ተዋናይ ሆኖ መገኘት አለበት›› በማለት ለሙያው ያለውን ታማኝነትና አመለካከት ይገልጻል።

> **ሄኖክ በትያትር ሙያ ውስጥም እያለ በተለያዩ ፊልሞች ላይ፣ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ይሰራል። ከዚህም በተጨማሪ ሄኖክ የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና ቶክሾዎችን ይመራል**

ሄኖክ በአሁን ሰዓት ‹‹የሌሊት ሙሽሮች›› የተሰኘ ትያትር በየሳምንቱ ሐሙስ፣ "የሚስቶቹ ባሎች" ትያትር እንዲሁ በዓለም ሲኒማ የሚሰራባቸው ትያትሮች ናቸው ። በየሳምንቱ በተመሳሳይ ቀን እና ሰዓት በቦታው ተገኝተው ተመልካች ፊት የትወና ብቃታቸውን ይዘው ይቀርባሉ። ይህ ትልቅ የሥራ ሥነ-ምግባርን የሚጠይቅ ነው። ‹‹የትያትር ሙያን ከሌሎች ሙያዎች ለየት የሚያደርገው ይህ ነው። ሐሙስ ቀን ትያትር የሚያሳይበት ሰዓት በመሆኑ ሐሙስ ሐሙስ ምንም ዓይነት ፕሮግራም አልይዝም። ትያትሩ ሁለት ዓመትም ሊታይ ይችላል። ነገር ግን የእይታ ጊዜው እስኪያበቃ ድረስ እዚሁ እገኛለሁ።›› የሚለው ሄኖክ ከዚህም በተጨማሪ ረቡዕ ረቡዕ የሚታይ "የሚስቶቹ ባሎች" የተሰኘ ትያትር እንዲሁ አለው ይህንንም ቀን አክብሮ በቦታው እየተገኘ ለተመልካቾቹ ያቀርባል።

ትያትር ሁልጊዜም ከተመልካች ፊት የሚቀርብ በመሆኑ ለተመልካች የተለየ ስሜት የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለተዋንያንም ሁልጊዜም አዲስ ይሆናል። ‹‹የትያትርን ሙያ ለየት የሚያደርገው ነገር ሁሌም ለምንሰራው ትያትር መድረክ ላይ ወጥቼ ትያትሩን እስክጀምረው ድረስ ልዩ የሆነ ፍርሃትን ይፈጥርብኛል። 40 ትያትሮችን ብሰራም 41ኛው ላይ ሊያስፈራን ይችላል። ይህ ስሜት ግን ወደ መድረክ ወጥቼ ማውራትና ከተመልካች ጋር መዋሀድ ስጀምር የሚጠፋ ስሜት ነው።›› በማለት ይህ ስሜት በእርሱ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ተዋንያን ላይም የሚከሰት ነገር እንደሆነ ያነሳል።

ትያትሩ ላይ ቆየት ያለ ጊዜን ካሳለፈ በኋላም ወደ ፊልም ሙያ መግባቱ አልቀረም። አንድ ከሀገረ አሜሪካ የመጣ ሰው ፊልም መሥራት ይፈልግ ነበርና ሄኖክም በዚህ ፊልም ላይ ለመሳተፍ ኦዲሽን ፈተናውን ወሰደ። የፊልሙ ርዕስ ‹‹ላቭ ዶት ኮም›› የሚል የመጀመሪያ ፊልሙን ለመሥራት ቻለ። ጊዜው ትንሽ ቆየት ስለማለቱም ይገልጻል ። ከዚያ በኋላ ‹‹ ውርስ ›› የተሰኘ ድራማ ሰራ። ትያትር መስራቱንም ቀጠለ። ሄኖክ ከፊልምና ከሥራዎቹ ባሻገርም በቴሌቪዥን ድራማዎቹ እንዲሁ ወደ ተመልካች መቅረቡን ቀጠለ። በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅ የነበረውን "ገመና" የቴሌቪዥን ድራማ አንድ እና ሁለት፣ የ"መለከት" ድራማ፣ "ያልተሄደበት መንገድ" የተወነባቸው የቴሌቪዥን ድራማዎች ናቸው። አሁን በቅርቡ ፋና ቴሌቪዥን ላይ "የሚጀመር "ማረፊያ" የሚል ድራማ ላይም በተዋናይነት ተሳትፏል።

ትያትር አስቀድሞ የተሳበበት እና ሥራውን የጀመረበት ሙያ ይሁን እንጂ፣ ኪነጥበብ ቦታው ሰፊ በመሆኑ ፊልም እና የተለያዩ ሥራዎችንም ይሰራል። ነገር ግን፣ ሄኖክ ትያትር ከእነ አስጨናቂነቱ እና ኃላፊነቱ ጭምር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ‹‹ለፊልም ሥራም ቢሆን ክብር አለኝ። እውነት ለመናገር ግን ትያትር ይበልጥ ያዘነብልብኛል። ፊት ለፊት ቁጭ ብሎ የሚያየኝ ሰው ላይ የያዝኩትን ስሜት ማስተጋባት አለብኝ። ምክንያቱም ፊት ለፊት፤ ግንባር ለግንባር ገጥመን ነው የምንተያየው። እያንዳንዱ እቅስቃሴያችንን ይመለከቱታል።›› ይላል ለዛም ይመስላል ረጅም ዓመታትን በትያትር ቤት ውስጥ ለመቆየት የቻለው። ፊልም፣ ትያትር፣ የቴሌቪዥን ድራማ፣ የተለያዩ ፕሮግራሞችን መምራት በእነዚህ ሁሉ ውስጥ ሄኖክ አለበት።

ኪነጥበብ የአንድ ሀገር ገጽታዋን የሚያሳይ ሲሆን፣ አሁንም ድረስ ግን በውስጧ ያሉ ባለሙያዎች የሚገባቸው ቦታ ያገኙ አይመስልም። በሙያው ውስጥ ፍቁሩ ኖሯቸው ለሚቆዩ ባለሙያዎች የልፋታቸውን ዋጋ አያገኙበትም ሲል ይገልጻዋል። ‹‹በዚህ ሰዓት ከአንድ ትያትር መግቢያ ዋጋ ይልቅ የአንድ ማኪያቶ ዋጋ ይበልጣል›› ሲል ሁኔታውን ያስረዳል። "ሁኔታዎች ከሙያው መውጣትን ቢያስመኙም ፍቅሩ ግን ይህን ተቋቁሞ የማቆየት አቅም አለው" በማለት ይገልጻል። እርሱም ይህን መርጧል።

በትያትር ሙያ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ያን ያህል ተከፋይ አይደሉም የሚለው ሄኖክ የኮቪድ ወቅት ለነዚህ ባለሙያዎች በጣም ፈታኝ እንደነበር ያስታውሳል። ምክንያቱም በጊዜው ትያትር መታየት ቆሞ የነበረ ሲሆን፣ ባለሙያዎችም ሌላ የገቢ ምንጭ አልነበራቸውም። ‹‹ትያትር ለብቻ የሚሰራ ነገር አይደለም፤ በቡድን የሚሰራ ነው። ጊዜው ደግሞ ያንን የሚፈቅድ ባለመሆኑ ብዙ ባለሙያዎች፣ እኔንም ጨምሮ ተፈትነዋል። ነገር ግን የትያትር ሙያው ተትቶ የሚተው አይደለም›› ሲል ያስታውሳል።

ሄኖክ በትያትር ሙያ ውስጥም እያለ በተለያዩ ፊልሞች ላይ፣ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ይሰራል። ከዚህም በተጨማሪ ሄኖክ የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና ቶክሾዎችን ይመራል። ከዚህ ቀደም በኢቢኤስ ቴሌቪዥን ይተላለፍ የነበረ መዝናኛ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ‹‹የአፍታ ጨዋታ›› ፕሮግራምን፤ በአሁን ሰዓት ደግሞ በፋና ቴሌቪዥን የሚተላለፍ ‹‹ጥበብ በፋና›› የተሰኘ ፕሮግራም ይመራል። እነዚህ ሥራዎችም ሌላ የገቢ ምንጭ እንደሆኑለት ይናገራል።

ሄኖክ የተለያዩ ድራማዎች፣ ፊልም፣ ትያትር ላይ የተለያዩ ገጸ-ባህሪዎችን ወክሎ ተጫውቷል። የግጥምጥሞሽ ጉዳይ ነው ብሎ የሚገልጸው ግን በተደጋጋሚ ዳያስፖራ ሆኖ የተጫወተውን ነው። ‹‹ዋትስ አፕ እና ቤተሰቡ›› የደራሲና ዳይሬክተር ኃይሉ ፀጋዬ ሥራ የሆነው ትያትር ላይ ዳያስፖራ ሆኖ ተጫውቷል። ይህም በዚህ ትያትር ብቻ ሳያበቃ በሌሎች ፊልሞች ላይም እንዲሁ ዳያስፖራ ሆኖ ተውኗል። ሄኖክ ሙያው በየእለቱ፣ በየሥራዎቹ የተለያዩ አዳዲስ ልምዶች የሚቃኙበት በመሆኑ ሙያው በራሱ በብዙ ገጠመኞች የተሞላ መሆኑን ያነሳል።

ሄኖክ በአንድ ወቅትም በሠራውና ‹‹ቤተሰቡ›› በተሰኘ ትያትሩ ተወዳድሮ አንደኛ ደረጃን ይዞ የወርቅ ሜዳልያ እና የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶለታል። በ1995 ዓ.ም እንዲሁ ተስፋ ኢንተርፕራይዝ ባዘጋጀው የትያትር ፌስቲቫል ላይ በነበረው የትያትር ውድድር አሸናፊ ነበር።

ሄኖክ በዚህ የኪነጥበብ ሙያ ውስጥ ከተማሪነት ጊዜው አንስቶ ከ30 ዓመት በላይ ቆይቷል። በቅርቡ የሚወጣ ‹‹ትዝታና ፍቅር›› የተሰኘ አዲስ ፊልም ይዞ እንደሚመጣ ተናግሯል። ወደፊትም የራሱን ትያትር ፕሮዲውስ የማድረግ (የማዘጋጀት) እቅድ እንዳለው ይናገራል። ሄኖክ በአሁን ሰዓት በዓለም ሲኒማ እየታየ የሚገኘው ‹‹የሚስቶቹ ባሎች›› ትያትር ላይ እየሰራ ይገኛል። ትያትሩ በፕሮዲውሰርነት የተሳተፈበት ሥራ መሆኑንም አንስቷል። በቅርቡ ደግሞ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን አንድን ትያትር ለእይታ ለማቅረብ በሂደት ላይ ይገኛል። ከትወና ባሻገር በቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በማቅረብ የተለያዩ መድረኮችን የሚመራ ሲሆን፣ የራሱ መዝናኛ ላይ ያተኮረ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ማዘጋጀት እንዲሁ በእቅዱ ውስጥ ያለ ሙያዊ ሥራ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳን ጦር መሪ ቡርሃን ከተፋላሚያቸው ጋር “እርቅ አይኖርም” አሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሱዳን ጦር መሪ ጀነራል አልቡርሃን ከፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች ጋር “እረቅ አይኖርም” ብለዋል።

አል ቡርሃን በጦሩ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መካከል ለዘጠኝ ወራት እየተካሄደ ያለውን ጦርነት እንደሚቀጥሉ በትናንትናው እለት ዝተዋል።

የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መሪ መሀመድ ሀምዳን ደጋሎ ወይ ሄሜቲ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ በሲቪል ጥምረቱ በቀረበው የተኩስ አቁም ሃሳብ ላይ ተስማምተው ነበር።

አሜሪካ የሱዳን ጦር እና ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች የጦር ወንጀል ፈጽመዋል ሰትል ከሳቸዋለች።

ነገር ግን የሱዳን ጦር መሪ አል ቡርሃን አማጺ ሲሉ የጠሯቸው “ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች በዳርፉር እና በተቀረው የሱዳን አካባቢ የጦር ወንጀል እየፈጸሙ መሆናቸውን መላው ዓለም ታዝቧል። በዚህ ምክንያት ከእነሱ ስምምነት አይኖርም።” ብለዋል።

በፈረንጆቹ 2023 ሚያዝያ አጋማሽ ላይ የተጀመረው ጦርነት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እንዲገደሉ እና 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ ከቤታቸው እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኗል።

ባለፈው ወር የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጥምረት የሆነው ኢጋድ የሁለቱን ጦር መሪዎች በአካል ለማገናኘት ጥረት ሲያደርግ ነበር።

ነገር ግን ቡርሃን ባለፈው ዓርብ እለት ተቀናቃኛቸውን ሄሜቲን “ከሀዲ” እና “ፈሪ” በማለት ለመገናኘት ፍቃደኛ እንዳልሆኑ ገልጸዋል።

ቡርሃን፣ ሄሜቲ በአዲስ አበባ የፈረሙትን የተኩስ አቁም ስምምነት ውድቅ አድርገዋል።

ሄሜቴ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አብደላ ሀምዶክ ከሚመራው ከሲቪል አስተዳደሩ ጥምረት ጋር በአዲስ አበባ በነበራቸው ስብሰባ፣ ንግግር ተካሂዶ ተኩስ ለማቆም ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው ነበር።

ቡርሃን ሄሜቲን እንደሀገር መሪ ተቀብለዋል ያሏቸውን ደቡብ አፍሪካን፣ ኢትዮጵያን እና ኬንያን ተቃውመዋል።

ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ባለፈው ወር ከሱዳን በምስራቅ አቅጣጫ የምትገኘውን ገዚራ ግዛት ከያዘ እና መንደሮች ከተዘረፉ በኋላ ከባድ ሕዝባዊ ተቃውሞ ገጥሞታል።

ቡርሃን ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎችን መዋጋት ለሚፈልግ ሱዳናዊ እንደሚያስታጥቁ ተናግረዋል።

አሜሪካ እና ሳኡዲ አረቢያ ሁለቱን ተፋላሚ ኃይሎች ለማስታረቅ ያደረጉት ጥረት ውጤት አላስገኘም።



ቡርሃን፣ ሄሜቲ በአዲስ አበባ የፈረሙትን የተኩስ አቁም ስምምነት ውድቅ አድርገዋል

## ፍቅረኛውን የገደለው ኦስካር ፒስቶሪየስ ከዓመታት እሥር በኋላ በአመክሮ ተለቀቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የፓራሊምፒክስ ተወዳዳሪ የነበረው ደቡብ አፍሪካዊው ኦስካር ፒስቶሪየስ ፍቅረኛው ሪቫ ስቲንካምፕ ከገደለ ከ11 ዓመታት በኋላ በአመክሮ ተለቀቀ።

ባለሥልጣናት እንደገለጡት ኦስካር 13 ዓመት ተፈርዶበት ከግማሽ በላይ እሥር ቤት ከቆየ በኋላ ዓርብ ንጋት “ቤት ተመልሷል።”

የስቲንካምፕ እናት ገዳዩ ኦስካር መለቀቁ ቅር ባያሰኛቸውም “ዕድሜ ልክ ቅጣት የተቀጣው ግን ቤተሰባችን ነው” ብለዋል።

አሁን 37 ዓመት የሞላው ኦስካር በአውሮፓውያኑ 2013 ነበር ፍቅረኛውን ከበር ጀርባ በሽጉጥ ደጋግሞ መትቶ የገደላት።

ሁለት እግር የሌለው ኦስካር ምርመራ ሲደረግበት ዘራፊ መስሎት በሽጉጥ እንደገደላት ገልጿል።

ኦስካር በአውሮፓውያኑ 2015 በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ፍርድ ቤት በእሥር እንደቀጣው ይታወሳል።



በደቡብ አፍሪካ ሕግ መሠረት ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ወንጀለኞች በአመክሮ ለመለቀቅ ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው።

ጥፋተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከተፈረደባቸው ጊዜ ግማሹን ካገለገሉ በኋላ በአመክሮ ሊለቀቁ ይችላሉ።

ኦስካር ፒስቶሪየስም ከተፈረደበት 13 ዓመት መካከል ከግማሽ በላይ እሥር ቤት ከርሞ ቢወጣም የቀረውን ጊዜ በጥብቅ ሕግና በተወሰነ መብት መንቀሳቀስ ይችላል።

በዚህ መሠረት ለተወሰኑ ሰዓታት ከቤት መውጣት አይችልም አልፎም አልኮል መጠጣት አይፈቀድለትም። ለሚዲያ ቃሉን መስጠትም ሕግ አይፈቅድለትም።

ከዚህ በተጨማሪ ፆታዊ ጥቃት እና ንዴትን ለማስታገስ የባለሙያ ምክር ማግኘት ይኖርበታል።

ኦስካር ከእሥር ቤት ከወጣ በኋላ በዋና ከተማዋ ፕሪቶሪያ በሚገኘው የአጎቱ መኖሪያ ቤት እንዳረፈ ተሰምቷል።

አትሌቱ እሥር ቤት ሳለ የማረሚያ ቤቱን ቅጥር ግቢ አረም በማሸን በመንቀል፣ ቤተ-መፃሕፍት በመሥራት እና የታራሚዎችን መፀዳጃ ቤት በማፅዳት አገልግሏል።

የማኅበረሰብ አገልግሎት ሰጪዎችና የሥነ-ልቡና ባለሙያዎች ኦስካር የፀባይ ለውጥ እንዳሳየ መስክረዋል።

የሟች እናት ጁን ስቲንካምፕ ኦስካር በአመክሮ ከእሥር ቤት ሊለቀቅ እንደሚችል ቤተሰቡ እንደሚያውቅ ተናግረዋል።

እናት “ምንም ቢሆን ልጃችን ተመልሳ እስካልመጣች ድረስ ፍትሕ ሰፍኗል ብለን አናስብም” ሲሉ ኦስካር ፍርዱን ቢያገለግልም ልጃቸውን መልሰው ማግኘት እንደማይችሉ ተናግረዋል።

ኦስካር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እሥር ቤት ያቀናው በአውሮፓውያኑ ጥቅምት 2014 ነበር። በ2015 እና 2016 መካከል ለተወሰነ ጊዜ ከእሥር ቤት ተለቆ በቁም እሥር ቆይቶ ነበር።

ኦስካር ሁለት እግሮቹን ያጣው ገና አንደኛ ዓመቱን ሳይደፍን ነበር። ነገር ግን ይህ ሳይበግረው በተቀጠለለት እግር ተጠቅሞ ውጤታማ አትሌት መሆን ችሏል።

በአትሌትነትን ዘመኑ በጣም እውቅና አግኝቶ “ዘ ብሌድ ራነር” የተሰኘ ስም አትርፎ ነበር።

ፒስቶሪየስ በፓራሊምፒክ ውድድር በርካታ ሜዳሊያዎች ከሰበሰበ በኋላ በ2012 የለንደን ኦሊምፒክ ተፈጥሯዊ እግር ካላቸው ሯጮች ጋር ተወዳድሯል።

ከስድስት ወራት በኋላ ፍቅረኛውን መግደሉ ተሰምቶ የዓለም መገናኛ ብዙኃን መነጋገሪያ ሆኖ ቆይቷል።

ፍቅረኛው ሪቫ ስትገደል 29 ዓመቷ ነበር። የሕግ ምሩቅ የነበረችው ሪቫ ውጤታማ ሞዴል እና የቴሌቪዥን ፕሮግራም አስተዋዋቂም ነበረች።


## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 205/1 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0045579582 ትግስት ታፈሰ ገብረማርያም በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተርን ኦቨር ታክስ /ቲኦቲ/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 251 እስከ 0300 እና ከቁጥር 0301 እስከ 0350 ሁሉም የተሰራበት ስለጠፉብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፉ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ትግስት ታፈሰ ገብረማርያም**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0041410814 ሀይለማርያም ሀብታሙ ደሳለኝ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ የፈፀምንበት የግዥ ደረሰኝ ዓመታዊ ግብር የተከፈለበት የሦስት ወር ሪፖርት የሚደረግበት ፋይል በጠቅላላ ማለትም የ2012 ዓ.ም. 2013 ዓ.ም. 2014 ዓ.ም. ሁሉም የተሰራበት በፋይል ቦክስ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፉ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሀይለማርያም ሀብታሙ ደሳለኝ**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

1.የአመልካች ስም፡ Siemens Healthcare Diagnostics Inc. አድራሻ፡ 511 Benedict Avenue, 10591, Tarrytown, UNITED STATES OF AMERICA
2. የማመልከቻ ቀን፡ 03/08/2022 እ.ኤ.አ
3. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/13625
4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ፡ የቃል
5. የንግድምልክት፡ URITEST
6. ቀለም፡ ጥቁር እና ነጭ
7. ዓለም ዓቀፍ ምድብ፡ 5
8. ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች፡
**ምድብ 5፡** የሰውነት ፈሳሾችን ለመተንተን የኬሚካል ሪጀንት ሙከራዎች

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዘገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-118 28/4/2016 (7/1/2024)

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ


1.የአመልካች ስም፡ International Association of Better Business Bureaus, Inc. አድራሻ፡ 4250 North Fairfax Drive, Suite 600, Arlington, Virginia 22203, United States of America 2. የማመልከቻ ቀን፡ 01/09/2022 እ.ኤ.አ
3. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/013814 4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ፡ የቃል እና የምስል
5. የንግድምልክት፡ BBB BETTER BUSINESS BUREAU
6. ዲስክሌመር፡ “BETTER BUSINESS BUREAU”
7. ቀለም፡ ጥቁር እና ነጭ 8. ዓለም ዓቀፍ ምድብ፡ 35
9. ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች፡ በማጭበርበር፣ በማሳሳት እና በጎጂ የንግድ ተግባራት መስክ የንግድ ሥራ ምርመራ አገልግሎቶች; በግል ልምዶች ላይ ተመስርተው በኩባንያዎች ላይ ቅሬታዎችን ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርቡ ድር ጣቢያ መስጠት; ከኩባንያዎች ጋር የንግድ ሥራ አለመግባባቶችን ለመፍታት ለተጠቃሚዎች የመስመር ላይ ቅሬታ ስርዓት መስጠት; በግል ልምዶች ላይ ተመስርተው የኩባንያዎች ግምገማዎችን ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርቡ ድር ጣቢያ መስጠት; የኩባንያዎች ደረጃዎችን የሚያሳይ ድር ጣቢያ ማቅረብ; ለሸቀጦች እና አገልግሎቶች ገዥዎች እና ሻጮች የመስመር ላይ የገበያ ቦታን የሚያሳይ ድረ-ገጽ ማቅረብ; ለገዢዎች የሸቀጦች እና አገልግሎቶች ሻጮችን ለማግኘት እና ለመመርመር በመስመር ላይ፣ ሊፈለግ የሚችል ማውጫን የሚያሳይ ድረ-ገጽ ማቅረብ፣ ለሸቀጦች እና አገልግሎቶች ገዢዎች እና ሻጮች የንግድ ዜና እና መረጃን በምርጥ የንግድ ልምዶች፣ የንግድ ማጭበርበሮች እና የማጭበርበር ማንቂያዎች፣ የሸማቾች ምክር እና ለንግድ ቤቶች ምክር መስጠት፣ ለሸማቾች አላግባብ የማስታወቂያ ዘዴዎችን እና የተሳሳቱ ምርቶችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ድር ጣቢያ ማቅረብ; በምርጥ የንግድ ልምዶች ርዕስ ላይ ለተጠቃሚዎች እና ለንግድ ድርጅቶች ትምህርታዊ መረጃ መስጠት; ስለ ምርጥ የማስታወቂያ ልማዶች እና በቪዲዮዎች፣ ጥያቄዎች፣ መጣጥፎች እና የመረጃ መረጃዎች ባህሪ ውስጥ አጎሳቋይ እና አጭበርባሪ የማስታወቂያ ልማዶችን እንዴት መለየት እና ማስወገድ እንደሚቻል ለሸማቾች እና ንግዶች ትምህርታዊ መረጃ መስጠት።

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዘገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-118 28/4/2016 (7/1/2024)

# ስፖርት



# የዋልያዎቹ ወርቃማ ኮከብ ስንብት

ቦጋስ አበበ

መነሻው ኮረም ሜዳ ነው። ውቢቷ ሀዋሳ በኮረም ሜዳ አቧራዎች ካፈራቻቸው የእግር ኳስ ፈርጦችም አንዱ ነው። በተስጥኦ የዳበረ አጥቂዎችን ከግብ እንደ ልብ የሚያገናኘው ምርጡ የጨዋታ አቀጣጣይ ሽመልስ በቀለ ጌዶ። ኳስን ሜዳ ላይ በጥበብ ሲያንከባልል ያምርበታል። ፈጣን፣ ብልጥ እና አመለ ሸጋም ነው።

ለዓመታት በወጥ አቋም በኢትዮጵያ እግር ኳስ የደመቀው ሽመልስ በቀለ ከኮረም ሜዳ እስከ ፈረሰኞቹ ቤት ቅዱስ ጊዮርጊስ ከዚያም ከወርቃማው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ትውልድ የአፍሪካ ዋንጫ ዐሻራ ጋር በከፍታው የደመቀው ኮከብ ለ15 ዓመታት ከተጫወተለት የብሔራዊ ቡድን ቆይታው ከቀናት በፊት ራሱን አግልሏል።

ከግብጽ የተለያዩ ክለቦች ውጤታማ የዓመታት ፕሮፌሽናል እግር ኳስ ሕይወቱ ማግስት በአንጋፋው መቻል በኳስ ሕይወቱ አመሻሽ ከላቀ ተጽእኖው ጋር ዛሬም የቀጠለው ኮከብ ባለፈው ሐሙስ በቅዱስ ጊዮርጊስ እና መቻል የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታ አዳማ ላይ ታላቅ ግልጋሎት ከሰጠበት የእናት ሀገሩ እግር ኳስ ስፖርት ድንቅ ማስታወሻውን እንደተወ በክብር መለየቱንም ይፋ አድርጓል። ከደቡብ አፍሪካ እስከ ካሜሩን በሁለት የአፍሪካ ዋንጫዎች ከአይረሴ ትውስታዎቹ ጋር ያንጸባረቀው ኮኮብ ሳይተካም ከዋልያው ተለይቷል።

ዋልያዎቹ ጥቅምት 4/2005 ዓ.ም ሱዳንን ድል አድርገው ከ31 ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ሲመለሱና ደቡብ አፍሪካ ላይ የማይረሳውን ድንቅ እንቅስቃሴ ሲያሳዩ ሽመልስ በወርቅ ቀለም የተጻፈ የታሪክ ዐሻራ ነበረው። ከካይሮ የክለብ እግር ኳስ ሕይወት የተሳካ ቆይታ እስከ ካላባር ናይጄሪያ የዓለም ዋንጫ ፍጥጫም ይህ የመሃል ሜዳ ኮከብ ነበረ። ከስምንት ዓመታት በኋላም የካሜሩን የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ ድረስ የኮረም ሜዳው ኮከብ ቁልፍ የዋልያዎቹ ኮከብ መሆኑን አስመስክሯል።



**በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ቁልፍ ተጫዋች ሽመልስ በቀለ፤**

ከአስደናቂው የዋልያዎቹ አጥቂ ሳላዲን ሰይድ እስከ አዳነ ግርማ፣ ጌታነህ ከበደ ከዚያም በአቡበከር ናስር የትውልድ ቅብብል ከድንቅ አጥቂዎች የማይረሱ ግቦች ጀርባ ሚስጥር የነበረው ይሄው ኮከብ ነው።

ከሀዋሳ የጀመረው የሽመልስ በቀለ የእግር ኳስ ጉዞ ማረፊያውን በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት አድርጎ ነበር። ወደ ሊቢያ ትሪፖሊ ተጉዞ፣ ሊቢያ ጦርነት ውስጥ በገባችበት ወቅት አስቸጋሪ ጊዜ አሳልፏል። ከዛም በሱዳን እና በግብጽ የተለያዩ ክለቦች ውስጥ ከተጫወተ በኋላ ዘንድሮ ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ ለመቻል እግር ኳስ ክለብ ፊርማውን አኑሯል።

በ15 ዓመታት የብሔራዊ ቡድን ቆይታው ለዋልያዎቹ በ83 ጨዋታዎች ላይ ተሰልፎ 16 ግቦዎችን ማስቆጥር የቻለ ሲሆን፤ 13 ለግብ የሚሆኑ ኳሶችን አመቻችቶ ማቀበልም ችሏል። አመለ ሸጋው አማካኝ አንዴ ቢጫ ካርድ የተመለከተ ቢሆንም ቀይ ካርድ ግን ተመዞበት አያውቅም ።

ዋልያዎቹን አምበልነት መምራት የቻለው ሽመልስ ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ ማግለሉን ‹‹ጊዜው አሁን እንደሆነ ይሰማኛል፤ ብሔራዊ ቡድኑን የምሰናበትበት ወቅት የምወደውን እና የምጓጓለትን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩን ሰንደቅ አላማ ወክዬ የምጫወትበት ጊዜ እንዳበቃ ይሰማኛል›› ሲልም ይፋ አድርጓል።

ኢትዮጵያን ለሁለት አፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ በማብቃት ደማቅ ታሪክ እና ትልቅ ዐሻራን ማሳረፍ የቻለው ሽመልስ ‹‹በቀጣይም ከሀገሬ እና ብሔራዊ ቡድኑ ጎን በመሆን በስሜት እና በኩራት ዋልያዎቹን የማበረታታ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ›› በማለትም ተናግሯል። አክሎም ‹‹ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻዋ ቀን በእኔ እምነቱ ኖሯችሁ ከጎኔ ለነበራችሁ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ›› ሲልም የስንብት መልዕክቱን አጋርቷል።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ቆይታው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ክብርን ያሳካው ሽመልስ፣ ከሀገር ውጭም በሊቢያ ለአሊተሃድ እና ለሱዳኑ ኤልሜሪክ መጫወቱ የሚታወስ ነው፡፡ በቀጣይም ወደ ግብጽ በማቅናት ፔትሮጀክት፣ ኤልጉና፣ ማስሪ ኤልመካሳ እና ኤን ፒፒ አይ ተጫውቶ አሳልፏል፡፡ ከአስር ዓመታት የውጭ ሀገር ቆይታ በኋላም ወደ ሀገሩ በመመለስ መቻልን የተቀላቀለው ዘንድሮ ነው።




# የገና በዓልን ከልጆች ጋር

እየሩስ ተስፋዬ

ልጆችዬ እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ። “እንኳን አብሮ አደረሰን!!!” አላችሁ አይደል? በጣም ጥሩ:: በዓሉ የሚመለከታችሁ እንዴት እያሳለፋችሁት ነው? መንፈሳዊ ቦታ በመሄድ፣ ዘመድ በመጠየቅ፣ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ሰብሰብ ብላችሁ እየተጫወታችሁ፣ እየተዝናናችሁ እና እየተደሰታችሁ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለኝም::

አንዳንድ የታደሉ ሰዎች ደግሞ ይህንን በዓል የታመሙ ሰዎችን፣ አቅመ ደካሞችን በመጠየቅ፣ በመርዳት፣ እና በማዝናናት በደስታ ያሳልፋሉ:: ልጆችዬ የገና በዓል በሀገራችን በደማቁ ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት መካከል አንዱ ነው:: ታዲያ ልጆችዬ የገና በዓል በሀገራችን በተለያዩ ክፍሎች በተለያዩ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ትውፊታዊ ክዋኔዎች በድምቀት ይከበራል:: በአብዛኞቹ ቦታዎችም በወጣቶች ጭፈራ፣ ደስታ፣ የገና ጨዋታ በመጫወት እና በመንፈሳዊ ዝማሬ እንደሚከበር ይታወቃል::

በዚህ በዓል ዘመድ ከዘመዱ፤ እንዲሁም ከጎረቤቱ ጋር በጋራ በመብላት፣ በመጠጣት፣ ቡና በማፍላት አቅም ያለው በግ፣ ፍየል፣ ዶሮውን ገዝቶ፣ ቤቱን አጽድቶ እና አስውቦ እንዲሁም ቅርጫ በመቃረጥ እንደሚያከበሩ ተመልክታችኋል ብዬ አስባለሁ:: እናም ልጆች እንደ ገና እና ሌሎች በዓላትን ጨምሮ በጋራ፣ በሰላም እና በፍቅር ሲከበር በባህላችን እንድንኮራ ያደርገናል:: ኧረ እንደውም ሁሌም ዓመት በዓል በሆነ ያስብላል አይደል?

ልጆችዬ ዶ/ር መጋቤ ሃዲስ ሮዳስ ታደሰ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልን ምክንያት በማድረግ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቴሌቪዥን ሥርጭት ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ ምን አሉ መሰላችሁ? ከወደ ምሥራቅ ሀገር በኮከብ ብርሃን ተመርተው የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ምክንያት በማድረግ ወደ ቤተልሔም የመጡት የጥበብ ሰዎች ሰብአ ሰገል ይባላሉ:: እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ ደስ ብሏቸው ወርቅ፣ እጣን እና ከርቤም አምጥተው ስጦታ አበረከቱለት::



**በገና ጨዋታ፣ አይቆጡም ጌታ**

በርካታ ሰዎች የገና በዓል ሲቃረብ ስጦታዎችን ሲገዙ አይታችኋል አይደል ልጆች? በሌላ በዓላት ላይ የማይስተዋለው የስጦታ መስጠቱ ተግባር፤ በገና በዓል ላይ ጎልቶ መታየቱን ሰበአ ሰገል ለኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታ ከመስጠታቸው ጋር የሚያያዝ ታሪክ እንዳለው የሃይማኖት አባቶች ይገልፃሉ::

ልጆችዬ ስጦታ መሰጣጣት በሰዎች መካከል ፍቅር፣ መከባበር፣ መተሳሰብ እንዲኖር ያደርጋል:: ታዲያ እናንተስ ምን ሰጣችሁ? ምንስ ተሰጣችሁ? ቸኮሌት፣ ከረሜላ፣ ኮፍያ፣ ጌጣ ጌጥ፣ መጽሐፍ እና የተለያዩ ነገሮች እንደተሰጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ:: ይህ ዓይነቱ ባህል መቀጠል የሚገባው ነው አይደል? ‹‹በሚገባ!!!›› አላችሁ? ጎበዞች።

ልጆችዬ ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› ሲባል ሰምታችኋል አይደል? ለምን ይመስላችኋል እንደዚህ የተባለው? የገና በዓል ከሃይማኖታዊ ትርጓሜው ባሻገር በማኅበራዊ ትስስር ላይ ሁሉም ሰው እኩል ሆኖ የሚደሰትበት፤ ጌታ እና ሎሌ እኩል ሆነው የሚያሳልፉት እንደሆነ ለማሳየት ነው::

በርግጥ የገና በዓል በተለያዩ ሀገራት ላይ በተለያዩ ዝግጅቶች መከበራቸውን ተከትሎ የባህል መኮራረጅ ይስተዋላል:: ልጆችዬ፣ የራስን ሳያውቁ የሌላውን አከባበርም ሆነ ባህል ለመኮረጅ፤ እንዲሁም ለማወቅ መጓጓት ተገቢነት አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ‹‹በፍጹም አናምንም::›› የሚል መልስ እንደምትሰጡኝ አልጠራጠርም:: እናም የገና ዛፍ፣ የገና አባት እና ሌሎችም የእኛ ባህል አይደሉምና እንዴት አድርገን የራሳችንን እንወቅ በሚለው ላይ መነጋገር ያስፈልጋል:: ለምሳሌ፣ በእኛ ሀገር በገጠሩ ክፍል ‹‹የገና ጨዋታ›› የሚባል አለ:: ስለዚህ ጨዋታ ምን ያህሎቻችሁ ታውቃላችሁ? ለምሳሌም በገጠሩ አካባቢ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ እረኞች የገና ጨዋታን ከታኅሣሥ ወር ጀምሮ እስከ ጥር እና ከዚያም እስከ ክረምቱ መግቢያ ይጫወቱት እንደነበር ይነገራል::

አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ሲጨዋወቱ እንደምትሰሙት፣ ሀገራችን የበርካታ ታሪክ እና ባህል ባለቤት ናት:: እናም ወላጆች፣ መምህራን እና ሌሎችን ስለታሪካችን፣ ባህላችን እና የዓውደ ዓመት በዓላት እንዴት መከበር እንዳለበት በመጠየቅ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻላችሁ ሀገራችሁን፣ ባህላችሁን እና ታሪካችሁን በሚገባ ውደዱ እንላለን:: ልጆችዬ፣ ዛሬ ዓውደ ዓመትም አይደል? ደስ ብሏችሁ ዋሉ:: ታዲያ ስትመገቡ፣ ስትጫወቱ፣ ስትጠጡ እና ከቦታ ቦታ ስትንቀሳቀሱ በጥንቃቄ እና በአግባቡ መሆኑን አትርሱ እሺ? ልጆችዬ በድጋሚ በዓሉ የሰላም፣ የደስታ እና የፍቅር እንዲሆንላችሁ በመመኘት በዚሁ እንሰነባበት::

**መልካም የገና በዓል!!!**